

**Rare glimpse** under the shroud allowed Giovanni Riggi of Turin, director of this experiment, Samuel Pellicori of the American team, and Luigi Gonella, a scientist representing the archbishop, to examine "blood" penetration **(above)**.

Narrowing the focus to millimeters with a photomicroscope, team member Mark Evans **(right)** produced the first photomicrographs of the shroud **(far right)** for close study of burns, "blood," and body image. Rust was probably left by a tack used in the 1931 exposition.


Whereas "blood" spread through the threads and was trapped in the crevices, the yellow stain of the body image is [illegible] segments. Had the image been forged using a hot statue, as some have suggested, high spots like the nose would show deeper scorches. Each stained fibril is an identical shade; the darker areas reflect only a greater number of stained fibrils. There is no evidence that color entered the fibrils as a gas or liquid, and there is no trace of pigment buildup.

Some of the scientists speculate there was nearly complete contact between a body and the cloth, and that sweat and body oil produced the image over an unknown period of time. Others feel there is stronger evidence that the image is faint scorch, but how it could be produced has not been determined.

ሳይንቲስቶች የከፈኑን ምሥጢር ለማወቅ የተለያየ ሙከራ ሲያደርጉ

# ትንሣኤ







**Pilgrims of science,** with white-glove care, anchored the shroud to a rotating frame designed for an exhaustive series of tests **(above)**. Organized as the Shroud of Turin Research Project, more than thirty Americans worked nonstop for five days alongside Italian scientists. An early discovery: "Blood" images, unlike body images, penetrate the shroud and are dense enough to be visible under back lighting **(right)**. But is it blood? Biophysicist John Heller, silhouetted before minute shroud fibrils **(above right)**, ran chemical and spectroscopic tests on fibrils and concluded, "It's hemoglobin." But he and other team members plan more tests.

የሳይንስ ሊቃውንት በልዩ ልዩ ዘመናውያን መሣሪያዎች እየተረዱ በጌታ መግነዝ ላይ ምርምር ሲያደርጉ ።



www.ethiopianorthodox.org

''ይህ መጽሔት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፡ ሥርዓትና ዜና ፡ ልማትና የግብረ ገብነት ትምህርት በተግባር ጭምር እንዲተረ ጐሙ ለሥራ እንነሣ የሚል ስለሆነ ''ትንሣኤ'' ተብሎ ተሰይሟል ።


አዘጋጅ
ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ
ም/አዘጋጅ ራደ አስረስ ።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ
ሐዋርያዊ ድርጅት
የሥነ ጽሑፍ ክፍል ተዘጋጅቶ
በወር አንድ ጊዜ
እየታተመ የሚወጣ ።

የስልክ ቁጥር 116616
የመልእክት ሣ.ቁ. 3137
አዲስ አበባ


መስከረም 1 ቀን 1978 ዓ.ም.( እ.ኤ.አ) ከታተመው ... ዊክ ከተሰኘው መጽሔት የተተረጐመ ስለመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መገነዝ የሚገልጽ ጽሑፍ በትንሣኤ መጽሔት ቁ.31 እና 34 አቅርበን እንደነበረ ይታወሳል ።

አሁንም በዚሁ በክርስቶስ መገነዝ የከፈን ጨርቅ ላይ የታሪክ ሰዎች ስለበሽታ የሚያጠኑ ሊቃውንት፡የቋንቋና የመጽሐፍ ቅዱስ ምሑራን ፡ የጨርቃ ጨርቅ ጠበብት ፡ ኬሚስቶች ፡ ፊዚስቶች ፡ የፎቶግራፍ ጠበብትና በሙቶ የሚቆጠሩ የከፈን ተረራማሪዎች እጅግ ጥልቅ የሆነና የተደጋገመ ምርምር ከአካሄዱ በኋላ ያገኙትን ውጤትና ያሰፈሩትን አስተያየት በሰኔ ወር 1980 ዓ.ም.(እ.ኤ.አ) ከታተመው ቁ.6 ናሽናል ጂኦግራፊክ ከተሰኘው እንግሊዝኛ መጽሔት ስለአገኘን ወደ አማርኛ ተርጉመን በዚህ እትም አውጥተነዋል ።

## ማውጫ

አርእስት ገጽ


ደብዳቤዎች ........
በራንጼ መታበዝ ብዙዎች ጳድቃን ......
ሳይንስ የከፈኑን ምስጢር ለማወቅ በመሯሩጥ ላይ ነው ......
የሕማማት ሳምንት ........
ምን እንርዳዎ ........
ብታውቂስ ሰላምሽ ዛሬ ነበር ........
ለምቀበርበት ቀን አሆናል ........
ምስጢረ ንስሓ ........
ምስት መስቀሎች በጎልጎ ........
በራሱ ሥልጣን ተነሣ ........
የቤተሰብእ ዓምድ ........
ይህን ያውቁ ኖረዋል? ........
ወላዲት አምላክ ........
የመጽሐፍ ቅዱስ ጥያቄ ......


## ደብዳቤዎች

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

አስቀድሜ የመጽሔቱ አዘጋጆች የእግዚአብሔር ቃል ለምዕመናን እንዲዳረስና ለመንፈሳዊ ዕድገታችንም የሚሆኑ ጠቃሚ ትምህርቶች እንድናገኝ ስለምታደርጉት ጥረት ምስጋናዬን ልገልጽ እወዳለሁ ።

ባለፈው ጥር ወር 1973 ዓ.ም. በቁ 40 መጽሔታችሁ ላይ ከአለቃ አያሌው ታምሩ ''ታቦትና ክብሩ'' በሚል ርዕስ የቀረበውን ትምህርት በጥሞና ተመልክቸዋለሁ የቀረበውም ሰፊ ገለፃ በጣም ጥሩ ነበር ።

ሆኖም፡- ''በሐዲስ ኪዳን ታቦት የለም'' የሚለውን ሃሳብ ለመቃወም በሰጡት አስተያየት የሐዋርያው ጳውሎስን መልዕክት 2ኛ ቆሮ .6ቁ.16 ሲጠቅሱ ፡ « የእግዚአብሔርን ታቦት በጣዖት ቤትየሚያኖር ማነው?ይላል ብለዋል ይሁንና በብዙ ትርጉሞች ፈልጌ ሀሳቡን ላገኘው አልቻልሁም ። አማርኛውም፡ « ለእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ከጣዖት ጋር ምን መስማማት አለው ? የሚል ነው ። ግዕዙም ቢሆን እሳቸው እንደጠቀሱት አይናገርም ታዲያ ትክክለኛውን አገላለጽ ቢያስረዱኝ?

በክርስቶስ ወዳጅዎ
ናዖግዚ ጽጌ

◦ ናዖግዚ ጽጌ ጥያቄዎን ለአለቃ አያሌው አቅርበን አለቃም የሚከተለውን መልስ ሰጥተዋል ።

1ኛ 2ኛ ቆሮንቶስ ም6 ቁ. 16 ''ወመኑ ዘይዴምር ታቦተ እግዚአብሔር ውስተ ቤተ ጣዖት » ይላል ግልጽ ነው። አያሳትትም አያጠያይቅም ። ''የእግዚአብሔርን ታቦት በጣዖት ቤት ውስጥ የሚያኖር ማን ነው?'' ማለት ነው ።

ስለምእመናን የተነገረ ነው የሚል ያኖር ይሆናል ። አይደለም ቀደም ሲሉ ያሉትን ቃላት መመልከት ቅን ልቦና ላለው ያስረዳል ''ጨለማን ከብርሃን ጽድቅን ከኃጢአት ክርስቶስን ከሰይጣን ምእመናንን ከመናፍቃን የሚያቀላቅል ማን ነው? ካለ በኋላ የእግዚአብሔርን ታቦት በጣዖት ቤት ውስጥ የሚያኖር ማን ነው ሲል ቅዱስ ጳውሎስ ጠይቋል ።

ተመላኪን ፡ አምላኪን ፡ የአምልኮት ምልክትን ለይቶ ያቀረበ ስለሆነ ማማታት አይቻልም ።

2ኛ '' ወእምዝ ተርኅወ መቅደሱ ለእግዚአብሔር ዘውስተ ሰማይ ወአስተርአየት ታቦተ ሕጉ እንተ ውስተ መቅደስ'' ራእይ 11 ፡ ቁ. 19 ''በሰማይ ያለ መቅደሱ ተከፈተ በመቅደሱም ውስጥ ያለች የሕጉ ታቦትም ተገለጠች ይላል ። ታቦት በሐዲስ ኪዳን እንኳን በዚህ ዓለም በሌላው ዓለም እንዳለ ያሳያል ።

3ኛ ጌታችን በመጽሐፈ ኪዳን በአንቀጽ 10 ስለቤተ ክርስቲያን ሥርዓቶች በሰጠው ትዕዛዝ ወውስተ ጽብሐዊ አረፍት ህየ ይኩን መካነ ምስዋዕ ብሎ የመንበረ ታቦትን አቀማመጥ ወስኗል ።

4ኛ በፍትሐ ነገሥት በፍትሕ መንፈሳዊ በአንቀጽ ቀዳማዊ ታቦት ቢሰበር እንደገና ማደስ እንደሚገባ ፡ ታቦትን ከቤት ማኖር እንደማይገባ ፣ ታቦት መሠዊያ እንደሆነ ታቦት ከቦታ ወደ ቦታ ሊዘዋወር የሚችል መሆን እንደአለበት ተጽፎአል ። ይህ ሁሉ ታቦት በሐዲስ ኪዳን ከሥራ ላይ ያለ መሆኑን ይገልጻል ። ጠያቂው ሊቀበሉት ፈቃድ ካላቸው ከዚህ ሌላ ምስክር አያሻም ።

× × ×

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

የካቲት 1973 በቁጥር 41 በወጣው መጽሔት ዲያቆን ብሥራት ፈያሳ በቤተ ክርስቲያናችን ስለሚያጋጥመን የጥዋፍና የዘቢብ እጥረት ያቀረበውን ጥያቄና የሰጣችሁትን መልስ በጥሞና ተመልክቸዋለሁ ።

እንደ እኔ አስተሳሰብ የጥዋፉን ችግር ለማቃለል በደብረ ታቦር ፡ ወረታ ባሕር ዳር ፡ ነቀምቴ ደሴ ፡ ጎሬ ፡ ጅማ ፡ ቁልቢ ፡ አዋሳና አዲስ አበባ ከተሞች ውስጥ አማካይ በሆኑ አብያተ ቤተ ክርስቲያናት የሚዘጋጅበትንና የሚከፋፈልበት ጣቢያ ቢቋቋም ፈትሉም ሰሙም የእኛው በሙሆኑ ሙሉ በሙሉ እንኳን ችግሩን ባናስወግደውም በሙቶ ዘጠና አምስቱን ማስወገድ እንችላለን ።

የዘቢብን ችግር በሚመለከት ረገድ ግን ከጠቅላይ ቤተ ክህነት በ1972 ዓ.ም. ወጥቶ የነበረውን ማስታወቂያ በመመልከት አንድ ሐሳብ ለአንድ ባለ ሥልጣን አዋይቼ ነበር ። ይጠቅማል በማለትና ሌላም የተሻለ ሐሳብ ከምእመናን ለመጠየቅ ከዚህ ቀጥዬ አቀርባለሁ ። መፍትሔውን ጊዜያዊና ዘላቂ መፍትሔ ብለን እንከፈለው ። ለጊዜያዊው መፍትሔ አሁን እንደሚያረገው ሁሉ ዘቢቡን ከውጭ አገር ገዝቶ በማስመጣት ለየአድባራቱ ማከፋፈል ነው ። መነሻውን ገንዘብም ከአዲስ አበባ አድባራትና ሌሎችም ሊከፍሉ ከሚችሉ በመዋጮ መልክ ለዚሁ ጉዳይ ብቻ በጠቅላይ ቤተ ክህነት ስም አዲስ አበባ በሚከፈት የባንክ ሒሳብ ውስጥ እንዲገባ ማድረግና የማስመጣቱን ሥራ መጀመር ። ተገዝቶ የሚመጣውንም ዘቢብ እያጠቡና በፕላስቲክ ከረጢት እያሸጉ ማከፋፈል ነው ። እዚህ ላይ አጠያያቂው ጉዳይ የማጠቡ ቴክኒክ ነው ለዚሁ ጉዳይ የተሠራ ልዩ መኪና ስላለ መኪናውንም ከእንግሊዝ ከእስፔይን ከቱሪክ እና ከግሪክ ማስመጣት ይቻላል ።

ይህ መኪና ቋሚ ንብረትና ፍጹም አስፈላጊ ስለሆነ ቤተ ክርስቲያናችን እንዲኖራት ያስፈልጋል ። የፕላስቲክ ከረጢቱም ሁለት ጥቅም አለው አንዱ ዘቢቡን በንጽሕና ለመጠበቅ ይረዳል ሁለተኛ ግን ከአንድ ኪሎ ግራ

ወደ ገጽ ፲፱ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

## ርእሰ አንቀጽ

# "በአንዱ መታዘዝ ብዙዎች ጻድቃን ይሆናሉ" ሮሜ.5፡19

የአንድ ሰው ቅን አገልግሎት ብዙዎችን ይጠቅማል በአንጻሩም የአንድ ሰው ስንፍና ብዙዎችን ሊጐዳና ሊያ
ከስር ይችላል በአንድ በረት ውስጥ አንድ ተዋጊ ከብት ከአለ መንጋው በሙሉ ሲታመስ ያድራል ፡ እንዲሁም በኑ
ንድ ማኅበር /ኅብረተሰብእ/ ውስጥ በመጥፎ ልማድና ጠባይ የተበከለ ሰው ማኅበሩን /ኅብረተሰቡን/ በሙሉ ይበክ
ላል ። ግን ራሱን ለግል ፍላጐትና ለጊዜያዊ ደስታ ያላስገዛ ፣ ፍቅርንና ትሕትናን ያወቀ ሰው ማኅበሩን በሚመራበ
ት ጊዜ የማኅበሩ አቅዋም የተስተካከለ ይሆናል ።

በአንድ በአዳም በደል ዓለም በሙሉ ለሞት ተዳርጐ ነበር በአዳም ስሕተት ምክንያት ሞት ወደ ዓለም መጣ ፡
ሮሜ. 5 ፡ 12 በአዳም ስህተት ምክንያት ኃጢአት ያልሠሩ ሁሉ በሞት ጥላ ሥር ኖሩ ። በአዳም አለመታዘዝ ምክን
ያት ብዙዎች ኃጢአተኞች ሆነው ኖሩ ፣ የአዳም ዓመፅ በዓለም ሁሉ የሞት ፍርድን አመጣ ።


ነገር ግን ከአዳም በደል ይልቅ የክርስቶስ ጽድቅ በዛ ፣ አዳም ለራሱ የማይገባውን ክብር ሲፈልግ በደለ ፡ በራ
ሱና በልጆቹ ላይ ሞትን አመጣ ። ክርስቶስ ግን ሞት ሳይገባው ለዓለም ቤዛነት ሞተ በሞቱም ሰዎችን አዳነ በአዳ
ም በደል ወደ ዓለም የገባው ሞተ ነፍስ በክርስቶስ ሞት ተወገደ ፣ በአዳም ለእግዚአብሔር ቃል አለመታዘዝ ምክን
ያት በዓለም ላይ ሰፍኖ የነበረው ኃጢአት ክርስቶስ "አባት ሆይ ይህች ጽዋዕ ከእኔ ትለፍ ነገር ግን አንተ እንደምት
ወድ ይሁን" በማለት በራሱና በአባቱ ፈቃድ ለሞት በመታዘዙ ተወገደ ። ማቴ. 26 ፡ 39 ።

በአዳም በደል ምክንያት ከእግዚአብሔር ጋር ተጣልቶና ርቆ የነበረው ዓለም በክርስቶስ ሞት ታረቀ ሠላት
ቱ ሳለን ከእግዚአብሔር ጋር በልጁ ሞት ታረቅን «ሮሜ .5 ፡ 13 አዳም ከፈጣሪው ይልቅ ራሱን ወደደ ፡ ራሱን ወዳደ
ከመሆኑም የተነሣ እምላክነትን በመሻቱ ወደቀ ተዋረደ ።

ክርስቶስ ግን ከራሱ ይልቅ ሰዎችን ወደደ የአዳም ልጆች ሁሉ ሕይወትን ያገኙ ዘንድ ሰዎችን ከመውደዱ
የተነሣ ራሱን አሳልፎ ለሞት ሰጠ « ነፍሱን ስለ ወዳጆቹ ከመስጠት ይልቅ ከዚህ የሚበልጥ ፍቅር ለማንም የለም »
ዮሐ. 15.13 ። እግዚአብሔር አብም ዓለምን ከመውደዱ የተነሣ አንድ ልጁን አሳልፎ ለሞት ሰጠ ። "በእርሱ የሚ
ያምን ሁሉ የዘለዓለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለ
ሙን እንዲሁ ወዶአልና ዓለም በልጁ እንዲድን ነው እንጂ በዓለም እንዲፈርድ እግዚአብሔር ወደ ዓለም አልላከው
ምና ። » ዮሐ 16

ክርስቶስ ወደ ዓለም ባይመጣ መጥቶም ባይሞት ሞቶም ባይነሣ ኑሮ ዓለም ሁሉ እንደ ተጐዳ በቀረ ነበር ነገር
ግን ዓለም እንደጠፋ እንዳይቀር የእግዚአብሔር ፈቃድ ሆነ ። ስለዚህም ክርስቶስ በመስቀል ላይ ተሰቀለ በመስቀል
ላይም የማዳን ሥራውን ፈጸመ የአንዱ የክርስቶስ አገልግሎትና መታዘዝ ለዓለም ሁሉ ጠቀመ ። የክርስቶስ ሞት ፡
ለዓለም ሕይወት የእርሱ ውርደት ለዓለም ክብር የእርሱ ሕማም ለዓለም ሰላም ሆነ "በሞቱ ሞትን አጠፋው
ተብሎ ተጽፎአልና ።

# ሳይንስ የከፈኑን ምሥጢር ለማወቅ በመፈለግ ላይ ነው



የክርስቶስን ምስል ይዞ የተገኘው የከፈን ጨርቅ እራፊ

የቱሪኑ ከፈን ብለው ይጠሩታል ምን አልባት አልሰማችሁ ይሆናል እስከ ቅርብ ዓመታት ድረስ ከኢጣልያ ውጭ ያሉ ሰዎች የሰሙት ጥቂት ናቸው ። ይህ ውድ የሆነ የበፍታ ጨርቅ በአሁኑ ጊዜ አወዛጋቢና አስቸጋሪ በመሆኑ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች ሁኔታውን በጥሞና እየተከታተሉ ናቸው በእርግጥ ይህ ነገር ምሥጢራዊና ታሪካዊ የሆነ በት ሳይንሳዊ ምርምር ስለ አተኮረበት ነው ።

ከዚህ ታሪክ በስተኋላ ያለው የታሪክና የአፈ ታሪክ ቅልቅል ከነገሥታት ከመሳፍንት ከመስቀል አርበኞችና ከ ጳጳሳት እንዲሁም ከኃይለኛ ጥራገ ነጠቆች ጋር የተያያዘ ይሆናል በማለት ምሥጢሩን ለመፍታት ከተሰማሩት ዘመናውያን ጠበብት መካከል የታሪክ ሰዎች ስለ በሽታ የሚያጠኑ ሊቃውንት የቋንቋና የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን የጨርቃ ጨርቅ ጠበብት ኬሚስቶች ፊዚስቶችና የፎቶግራፍ ጠበብት ይገኙበታል ።

ለጥያቄው ከተገኙት ፍንጮች ውስጥ አስደናቂ የሆኑት የሮማውያን መግረፊያ (ጅራፍ) የደረቁ የአበባ ብናኞች ከኢየሩሳሌም የመቃብር ቦታዎች የመጡ አጽሞችና በአሁኑ ጊዜ ጨረታንና ማርስን ለማጥናት በተዘጋጁ መሣሪያዎች የተነሡ ፎቶግራፎች ይገኙበታል።

ነገር ግን ከተገኙት ፍንጮች ውስጥ የሰው ሕሊና ሊደርስበት ያልቻለው በከፈኑ ላይ የሚታየው እጅግ ረቂቅና አስደናቂ ሙሉ አካል ዕርቃኑን የሆነ ጽሕማምና ረጂም ፀጉር ያለው የሰው ምስል ነው ።

ፊቱ ወይም ገጹ የሰው እጅ የተጠበበበት እንዳልሆነ ሲረጋገጥ በአናቶሚ ጥናት አካሉም ትክክለኛ ነው ። የሚያሳየውም አሰቃቂ የግርፋት ፣ የችንካር ፡ የመስቀል ፣ የመወጋት ምልክት ሲሆን የተወጋውም ምንአልባት በሾህና በጦር ሳይሆን አይቀርም ይህም በወንጌል ከ ተጻፈው ከናዝሬቱ ኢየሱስ ታሪክ ጋር ፍጹም ተመሳሳይ መሆኑን በትክክል ያስረዳል ።

በእርግጥ አንዳንዶቹ ከሁለት ሽህ ዓመታት በፊት ይህ የዝሆን ጥርስ አይነት (ነጭ) ቀለም ያለው የበፍታ ጨርቅ የአርማታው ዮሴፍ የክርስቶስን አካል ከፍኖ ከአለት በተወቀረው መቃብር ያስቀመጠበት በፍታ ነው ብለው አምነዋል ።

ተቀባይነት ያላቸው መዛግብት ርቀው አይርቁም ። ከፈኑ በመጀመሪያ የታየው (የተነሣው) በ14ኛው ምእት ዓመት በሊሬ ከተማ በፈረንሳይ ውስጥ ነው ። ባለቤቱም (ይዞት የተገኘው ሰው) ጆፈሬ ዶቻርኒ የተባለ በሊሬ የታወቀ አንድ ወጣት መኰንን ነበር የጦርነት እልቂት የሚያወራ ታሪክ ቢኖርም ሰውዬው ከየት እንዴት እንዳገኘው የሚያውቅ ሰው የለም ።

በአራተኛው የመስቀል ጦርነት ጊዜ የነበረው ሮበርት ደክላሪ የተባለው የታሪክ ጸሐፊ እ.ኤ.አ. በ1203 ዓ.ም. በቁስጥንጥንያ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ምስል የሚያሳይ መከፈኛ እንዳየ ጠቅሲል እንደገናም ከዓመት በኋላ በጻፈው ጽሑፍ የመስቀል አርበኞች የቢዛንታይን ከተማ ሲዘርፉ እንደ ጠፋ ገልጦአል ። የለሪ የተልባ እግር (የበፍታ) ጨርቅና የቁስጥንጥንያ መከፈኛ ተመሳሳይ ቢሆንም ኑሮ ምሥጢሩ ግን ከዶቻርኒ ጋር አብሮ ተቀብሮአል ።

የእንግሊዙ ጸሐፊ ኢያን ዊልሰን ምስል ያለውና የታወቀ አንድ የከፈን ጨርቅ ከኢየሩሳሌም ወደ ኢድሳ (የአሁኗ ኡርፋ በቱርክ የምትገኘው) ከዚያም ወደ ቁስጥንጥንያ በመጨረሻም ወደ ለሪ እንደ ገባ ያምናል ነገር ግን ዊልሰን ለሌሎች ለማስረዳት በሚያቀርባቸው መረጃዎች ያችገራልበብዙ ዓመታት ብዛት ያላቸው መከፈኛዎች

ወደ ገጽ ፳፱ዞል



www.ethiopianorthodox.org

# የሕማማት ሳምንት

አዳምና ልጆቹን ከሞት ወደ ሕይወት ከኀሣር ወደ ክብር ለማሸጋገር መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፀዋትወ መከራ የተቀበለባቸው ዕለታት የሕማማት ሳምንት ይባላሉ ዕለታቱም ከዓርበ ኒቆዲሞስ በኋላ ወይም ከሆሣዕና እሁድ እስከ ቅዳሜ ሥዑር የሚገኙት ዕለታት ናቸው ።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በነዚህ ዕለታት ልዩ ልዩ ፀዋትወ መከራን መቀበል ብቻ ሳይሆን ብዙ ትምህርቶችን አስተምሮአል በርኬት ያሉ ድንቅ ሥራዎችንም ሠርቶአል ።

የሕማማት መጀመሪያ በሆነው እሁድ( ሆሣዕና) በአህያ ተቀምጦ በድል አድራጊነት ወደ ኢየሩሳሌም ገባ ሕፃናትና ሽማግሌች የዘንባባ ዝንጣፊ ይዘው"መድኃኒት መባል ከዳዊት ወገን በሥጋ ለተወለደው አምላክ ይገባል » በማለት አዳኝነቱንና አምላክነቱን እየመሰከሩ ተቀበሉት ። ክርስቶስ በ አህያ ተቀምጦ ወደ ኢየሩሳሌም መግባቱ ልዩ ምሥጢር አለው ይኸውም፤በትንቢተዘካርያስ 9 ፡ 9 የተነገረው ትንቢት እንደ ተፈጸመ ለማስረዳት 2ኛ በአህያ የተቀመጠው ሰው ሌላውን አሳድዶ አይዝም እርሱም ሮጦ አያመልጥም ። ክርስቶስም በእምነት ለሚፈልጉት የማይታጣ ቅርብ ሲሆን በእምነት ለማይፈልጉት ግን የማይገኝ መሆኑን ያስረዳል ።

ሰኞ በቤተ መቅደስ ይሸጡና ይለወጡ የነበሩትን አባረረ ፤ ቤተ መቅደስ የጸሎት ቤት እንጂ የንግድ ቤት አለመሆኑን አስተማረ ። ፍሬ ያልተገኘባትን በለስ ረገመ በበለስ አንጻር ኃጢአትን ረገመ አስወገደ ። ሰኞ የተረገመችው በለስ ማክሰኞ ደርቃ ተገኘች በስምዖን ም ቤት ሳለ ማርያም እንተ ዕረፍት ዋጋው እጅግ ውድ የሆነ ሽቱ አምጥታ ቀባችው "ሽቱው በወርቅ ተሸጦ ለነደያን ቢመጸወት ባልተሻለም ነበር" በማለት ይሁዳ መዛሙርቱ ሲያጉረመርሙ «ነዳያን ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ይኖራሉ እኔ ግን ሁል ጊዜ ከእናንተ ጋር አልኖርምና መልካም አደረገች" አለ ዮሐ. 12 ፡ 3-8።ስለትንሣኤ ሙታንና ስለ ግብር አከፋፈል እንዲሁም ሥራውን ሁሉ በማን ሥልጣን እንደሚሠራ ከጸሐፍትና ከፈሪሳውያን ለቀረበለት ጥያቄ መልስ ሰጠ ።

ረቡዕአይሁድ ጌታን ለመግደል ቁርጥ ውሳኔ አደረጉ ። የጌታ ምክረ ሞት ተፈጸመ ። እንዴትም እንደሚይዙት ቀደም ብለው ከይሁዳ ጋር ተስማሙ። በዚህ ዕለት የጌታ ምክረ ሞት በመፈጸሙ አንጻር ድኅነተ ዓለም ተጀመረ ከዚህም የተነሣ ረቡዕ"ጾመ ድኅነት" በመባል በየሳምንቱ እንዲጾም ሆነ

ሐሙስ የመጨረሻውን የፋሲካ እራት ከደቀ መዛሙርቱ ጋር በላ ፤ ከእራት በኋላ መሥዋዕተ ኦሪትን ሽሮ መሥዋዕተ ወንጌልን ተካ ሥርዓተ ኦሪትን ለውጦ አዲስ ሥርአተ ቁርባን ሠራ ። ማቴ 26 ፡ 26 - 27 ። የደቀ መዛሙርቱን እግር አጠበ «ያደረግሁላችሁን ታያላችሁን?... እኔ ጌታና መምህር ስሆን እግራችሁን ከአጠብሁ እናንተ ደግሞ እርስ በርሳችሁ እግራችሁን ተጣጠቡ ዘንድ ይገባችኋል ። እኔ ለእናንተ እንዳደረግሁት እናንተ ደግሞ ታደርጉ ዘንድ ምሳሌ ሰጥቻችኋለሁ ።"

ዮሐ .13፡ 13 - 15 በማለት ትሕትናን አስተማረ ። በጌቴሴማኒ ጸለየ « ወደ ፈተና እንዳትገቡ ተግታችሁ ጸልዩ » ማቴ 26 ፡ 40 ሲል ጸሎት ሰዎችን ከልዩ ልዩ ፈተና እንደሚታደግ አስረዳ ይሁዳ ጌታችን ያሲያዘው ሐሙስ ማታ ነው ።

በአይሁድ እጅ ከገባ ጀምሮ እስከ ተሰቀለበት ሰዓት ድረስ ከአንዱ ሊቀ ካህናት ወደ ሌላው ቤት ሲመላለስ በሊቃነ ካህናቱና በሕዝቡ ፊት እየቆመ የሐሰት ምስክሮች "በሰንበት ድውይ ፈውሶ አለ ፤ የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ ብሎአል ፤ ቤተ መቅደስን አፍርሼ እንደ ገና በሦስት ቀን እሠራለሁ " ሲል ሰምተናል በማለት ደግ ሥራውን ክፉ ፤ ጻድቁን አምላክ ኃጥእ በማስመሰል ሲመክሩ አደሩ ።

ዓርብ ጥዋት የካህናት አለቆችና የሕዝብ ሽማግሌች በአንድነት ተሰብስበው ኢየሱስ ክርስቶስን አሥረው ወደ ገዡ ወደ ጲላጦስ አቀረቡት ክርስቶስ ሞት የሚገባው መሆኑንም ለጲላጦስ አስረዱ ሕዝቡ ሁሉ በአንድ ድምፅ "ሞት ይገባዋል" እያሉ እንዲጮሁ አስተባበሩ ። ጲላጦስ ክርስቶስን መረመረው ፤ ክርስቶስ ግን ምንም በደል የሌለበት ሆኖ ተገኘ ። ጲላጦስም እኔ ከዚህ ጻድቅ ሰው ደም ንጹሕ ነኝ እናንተ ተጠንቀቁ ሲል በሕዝብ ፊት እጁን ታጥቦ የክርስቶስን ጽድቅ መሰከረ ።

በቀትር ጊዜ (ስድስት ሰዓት) ክርስቶስ በሁለት ወንጀለኞች መካከል በመስቀል ላይ ተሰቀለ ከስድስት እስከ ዘጠኝ ሰዓት ዓለም በሙሉ ጨለማ ሆነ ሉቃ 23 ፡ 44 ፀሐይ ጠቆረ ጨረቃ ደም ሆነ ከዋክብት ረገፉ በዘጠኝ ሰዓት "አባት ሆይ ነፍሴን በእጅህ አደራ እሰጣለሁ" ሉቃ 23፡ 46 በማለት በራሱ ሥልጣን ቅድስት ነፍሱን ከቅዱስ ሥጋው ለየ ። በዚህም ጊዜ መንጦላዕተ ቤተ መቅደስ ከሁለት ተቀደደ ድንጋዮች ተከፋፈሉ ፤ ተፈረካከሱ መቃብራት ተከፈቱ ሙታን ተነሱ ።

ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሳለ ሰባት ተአምራት ተፈጽመዋል እነርሱም ፤ 1 . የፀሐይ መጥቆር 2. የጨረቃ ደም መሆን 3 የከዋክብት መርገፍ 4 የቤተ መቅደስ መጋረጃ መቀደድ 5 የድንጋዮች መፈረካከስ 6 የመቃብር መከፈት 73 የሙታን መነሳት ናቸው ። እነዚህ ሰባቱ ተአምራት በመባል የሚነገሩ ዓበይት ተአምራት ናቸው ።

ዓርብ ወደ ማታ ዮሴፍ የተባለ የአርማትያስ ተወላጅ ወደ ጲላጦስ ቀርቦ የጌታን ሥጋ ከመስቀል አውርዶ እንዲወስድና እንዲቀብር ጠየቀ ጲላጦስ የኢየሱስን ሥጋ ከመስቀል አውርደው ይሰጡት ዘንድ አዘዘ ። ዮሴፍም በንጹሕ ግምጃ ከፍኖ ቀበረው መለኮት በአካለ ሥጋ በመቃብር አደረ ፤ በአካለ ነፍስ ወደ ሲኦል ወርዶ አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን በግዞት ለነበሩ ነፍሳት ነፃነትን ሰበከላቸው 1ኛ ጴጥ.3 ፡ 18 - 19 ። በክርስቶስ ሕማመ ሥጋ የአዳም ልጆች ሕማመ ነፍስ ተወገደ ። በክርስቶስ ኃጥእ መባል የአዳም በደል ተሠረየ ። ክርስቶስ መከራ መስቀልን በመሸከሙ በአዳም ልጆች ትከሻ ላይ የነበረው ከባድ የኃጢአት ሸክም ከአዳምና ከልጆቹ ትከሻ ወረደ በክርስቶስ ሞት አዳም ከነልጆቹ ሕይወተ ነፍስን አገኘ ክርስቶስ ወደ መቃብር በመውረዱ አዳም ከነልጆቹ ከሲኦል ወጣ ። ረቡዕ የጌታ ምክረ ሞት ተፈደመ የአዳም ድኅነት ተጀመረ ዓርብ ጌታ ሞተ ተቀበረ አዳም ከነልጆቹ ከሲኦል ወጣ ከሞተ ነፍስ ዳነ ስለዚህ ረቡዕና ዓርብ ከበዓለ ሃምሳ በቀር በጾም ይከበራሉ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከምትቀበላቸው ሰባት አጽዋማት አንዱ ይኸው ጾመ ረቡዕ ወዓርብ ነው ። እርሱም ጾመ ድኅነት ይባላል ።

ይህ ሁሉ መከራ በክርስቶስ ላይ ሊፈጸም ባልተገባውም ነበር ግን ራሱ ክርስቶስ ለእኛ ቤዛ ይሆን ዘንድ ስለመጣ ሊቀበለው የማይገባውን ተቀበለ ሕመም ሳይኖርበት ታመመ ፤ መታሰርና መገረፍ ሳይገባው የኗሊት ታሠረ ፊቱን በጥፊ ጸፋት ምራቃቸውን ተፋበት ፤ ራሱን በዘንግ መቱት ይህን ሁሉ በሚያደርጉት ጊዜ ከቶ አልተቀየመም ከባሕርይ አባቱ ከአብ ይቅርታን ጠየቀላቸው እንጂ አልተበቀላቸውም በመስቀል ላይ በምሥማር ሲቸነከሩት በጦር ሲወጉት "አባት ሆይ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው" አለ ። ይህም አባባል ኃዳጊ በቀል መሆኑን ያስረዳል ።

ተከታዮቹ ክርስቲያኖችም የእርሱን ፈለግ ተከትለው ክፉ ለሚያደርግባቸው መልካም መመለስ እንደሚኖርባቸው ክርስቶስ ስለ እነርሱ የተቀበለውና የታገሠው መከራ ያስተምራል ይመስክራል ።"የተጠራችሁት ለዚህ ነውና ክርስቶስ ደግሞ ፍለጋውን እንድትከተሉ ምሳሌ ትቶላችሁ ስለ እናንተ መከራን ተቀበለ ። እርሱም ኃጢአት አላደረገም።ተንኮልም በአፉ አልተገኘም ሲሰድቡትም መልሶ አልተሳደበም መከራም ሲቀበል አልዛተም። ነገር ግን በጽድቅ ለሚፈርደው ራሱን አሳልፎ ሰጠ ለኃጢአት ሞተን ለጽድቅ እንድንኖር እርሱ ራሱ በሥጋው ኃጢአታችንን በእንጨት ላይ ተሸከመ። በመገረፉ ቁስል ተፈወሳችሁ እንደ በጎች ትቅበዘበዙ ነበርና አሁን ግን ወደ ነፍሳችሁ እረኛና ጠባቂ ተመልሳችኋል ።" 1ኛ ጴጥ 2 ፡ 21 - 25

አዎ የሰው ልጆች ሁሉ በአዳም በደል ጠፍተውና ተቅበዝብዘው ነበር አሁን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የጠፉት ተገኝተዋል የተበተኑት ተሰብስበዋል ። በኃጢአት ባርነት የነበሩት ነፃነት አግኝተዋል ።

ስለዚህ የሕማማትን ሳምንት ክርስቲያኖች ሁሉ በታላቅ መንፈሳዊ ሥነ ሥርዓት ያከብሩታል ፤ ሳምንቱ የሚከበረው ከብሉይና ከሐዲስ ኪዳናት ከሊቃውንት ስለ ክርስቶስ ሕማምና ሞት የሚናገሩትን መጻሕፍት በማንበብ በጾም ፤ በጸሎትና በስግደት ሲሆን ብዙ ክርስቲያኖች ይህን ሳምንት የሚያሳልፉት ጥሬ ቆርጥመው ውሃ ጠጥተው ወይም የጨው ቂጣ በልተው በመሬት ላይ ተኝተው ነው ። የላመ የጣመ አይቀምሱም በአልጋና በምቾት አይተኙም ። ይህም ሕማምና ሞት የማይገባው አምላክ ሰዎችን ከመውደዱ የተነሣ የተቀበለውን ፀዋትወ መከራ ለማስታወስ ፍቅሩንና ቸርነቱን በየጊዜው ለሚነሣው ትውልድ ለማስተማር ነው ።

ራዶ አስረስ

## ሳይንስ የከፈኑን .....

ከገጽ ፫ የዞረ

ግማሹ ምስል ያለው ሌላው የሌለው እውነተኛ የጌታ መግነዝ (ከፈን) እንደሆኑ ሆነው ቀርበው ነበር ። በተለይም በ14ኛው ምእት ዓመት በውሸትና በማጭበርበር የተሞላ የቅርሳቅርስ ንግድ በሰፊው ተስፋፍቶ ነበር ። ስለዚህ ነው እ.ኤ.አ. በ1389 የለሪ ከፈን ለኢግዚ. ቪሽን ሲቀርብ በትሮይ ጳጳስ መወገዙ የማያስደንቀው ።

ከርሱ በፊት በነበረው ሰውዬ ቀርቦ የነበረውን ክስ ጠቅሶ "ከጥያቄና ከምርምር በኋላ" ጨርቁ በሰው የተሣለ በውስጡም ያሉት ነገሮች በሠዓሊ የተቀቡ እንደሆኑ አምኖአል ።

ይህ ዳኝነት ለወደፊት የከፈኑን እውነተኛነት ላልተቀበሉት ሰዎች መከላከያ ለማዘጋጀት ነው ። ነገር ግን የአበጅኑን ጳጳስ ክሌመንት (ቀሌመንጦስ) ሰባተኛ የለሪ ጨርቅ የሰውነተኛው ከፈን ማስታወሻ ሆኖ እንዲቀመጥና መናንያንና ፍቅረ እግዚአብሔር ያላቸው ሰዎች እንዲጐበኙት ይቀመጥ ብሎ አዘዘ ።

. እ.ኤ.አ. በ1453 ዓ.ም. የዶቻርኒ የልጅ ልጅ ማርገሪት ከወላጆችዋ በውርስ ያገኘችውን ባልታወቀ ምክንያት ለሳቮይ መስፍን ለሉዊስ ሰጠችው ። በ16ኛ ምእት ክፍለ ዘመን ዳዊት ሶክስ በአስደናቂው መጽሐፍ (File on the shroud ) የከፈኑ ማኅደር በሚባለው ማርገሪት እንዴት እንደሰጠች ምክንያት ሲያቀርብ እንዲህ ብሏል "ጨርቁን ለልዑል ሉዊስ ልትሰጠው የቻለችው ወደ ባርጋንዲ ስትመለስ ከቻምበሪ በር) የሳቮይ ዋና ከተማ ላይ ስትደርስ ቅርሱን የያዘችው በቅሎ አልሄድም ብላ በማስቸገርዋ ነው " ብሎአል ።

የትኛውም ምክንያት ይሁን ከፈኑ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ የስቮይ ነው ። ልዑል ሉዊስ በቻምብሪ ቅዱስ ቻፒል የተባለ ቤተ ክርስቲያን አሠርቶ በክብር አስቀምጦት ነበር ።

በአሁኑ ጊዜ ለየት ተደርጐ እንዲታይ ያደረገው በ1532 ዓ.ም. በቻምብሪ ከተማ የደረሰው ሁኔታ ነው ። ከቅዱስ ቻፕል (ቤተ ክርስቲያን) በተልሔም በተነሣው የእሳት ቃጠሎ ከፈኑ ከመውጣቱ በፊት ሣጥኑ በመያያዙ መዳቡ ቀልጦ ከልብሱ ላይ ስለተንጠባጠበ የእጥፋቱ ጠርዝ ጠቁሮአል ። እሳቱንም ለማጥፋት ውሃ ስለፈሰሰበት ቀለሙ ደብዝዟል ።

ምንም እንኳን የተቃጠለው ክፍል በሌላ ጨርቅ ቢጣፍ የምስሉ አብዛኛው አካል ድኖአል ። እየቆየ ሲመጣ እሳቱ





www.ethiopianorthodox.org

በጣም ጠቃሚ የሆነ ፍንጭ አሳይቷል። ይህንንም ሳይንቲስቶች በአሁኑ ጊዜ እየተረጐሙት ነው ።

በ1578 የሳቮይ ልዑል ከፈኑን የአልፕስን ተራራ አቋርጦ ወደ ሰሜናዊው ምዕራብ ኢጣልያን ክፍል ፒድመንት ወደ ዋና ከተማይቱ ቱሪን ወስደው ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ድኖ እስከ አሁን አለ ።

ርእስ ዓለም ዓቀፍ ስብሰባ ላይ የተገኙትን ነጥቦች አወዳድረዋል ።

ለብዙ ጊዜ የቆየ ነገር ቅርጹን አስመስሎ የማቅረብ ጥበብና ሳይንቲስቶች ደግሞ በአስደናቂ ሁኔታ ቅሌቱን የማከሸፍ መንገዳቸውን ለማወቅ ፍላጐት ነበረኝ ይህ ፍላጐት በቱሪን የተደረገውን ስብሰባ ለመሳተፍና ምንአልባትም በክርስትና ዓለም የመጀመሪያው







የጌታ መግነዝ በሚጐበኝበት ቤተ መቅደስ የቱሪኑ ሊቀ ጳጳስ ሥርዓተ ቅዳሴ ሲመሩ ።

አራት መቶ ዓመት አለፈው እ.ኤ.አ. በ1978 ዓ.ም. ከፈኑ ወደ ቱሪን የገባበትን መታሰቢያ ዓመት ሲያከብር ለሕዝብ እንዲታይ ወጣ ። ለአርባ አምስት ዓመታት ያህል ለሕዝብ እንዲታይ አልወጣም ማለት በሃያኛው ምእት ዓመት አንድ ጊዜ ብቻ በ1931 ዓ.ም. ማለት ነው ለስድስት ሳምንታት ያህል ለኢግዝቢሽን በቀረበ ጊዜ ሦስት ሚሊዮን ጐብኝዎች ወደ ቱሪን ከተማ መጥተዋል ። ከእነዚህም ውስጥ ራሳቸውን(ሲንዶኖጂስትስ) ( Sindonologists ) ስለ ልብስ የሚመራመሩ ብለው የሚጠሩ በመቶ የሚቆጠሩ የከፈን ተመራማሪዎች ያገኙበታል ። እነርሱም ለሁለት ቀናት ያህል "ከፈኑና ሳይንስ" በሚል

ሊሆን የሚችለውን ቅርስ ለማየት መራኝ ። ይላሉ ዜና አቅራቢ ኬኔት ዌቨር ።

ደግሞም ወደ ቱሪን 36 አሜሪካኖችን የያዘ ቡድን 72 ሣጥን ዘመናውያን መሣሪያዎችና የከፈኑን ምሥጢር ለማውጣት ይረዳል ተብሎ ተስፋ የተጣለበት /ኤሌክትሮኒክ ጌር/መሣሪያ ይዘው መጥተዋል ።

በመጥምቁ ዮሐንስ ስም በታነጸው ካቴድራል እንደገባሁ ሰው ሠራሽ መብራቶች በጣም ደምቀው ጥላ እስከማይታይበት በርተው ነበር ። ከመሠዊያው ከፍ ብሎ ጥይት ከማይበሳው መሥታዎት በስተጀርባ ጥንታዊው የዝሆን ጥርስ አይነት ቀለም (ነጭ) መልክ ያለው

ከተልባ እግር የተሠራውን ጨርቅ ከ14 ጫማ ርቀት ላይ በጣም የሚንቦገቦገውንና የሚያንፀባርቀውን በመጀመሪያ ምንም አይነት መልክ አላየሁበትም ነበር ። ነገር ግን ደረጃውን ወጣሁና ወደ ላይ ዘወር እንዳልሁ በ ( Santa - sindone) በቅዱስ ከፈን" ፊት ለፊት ለብዙ መቶ ዓመታት ያህል ልዩ ሁኔታዎችን ልባዊ ተመስጦንና መወያያ መድረክ የፈጠረውን ምስል በግልጥ ማየት ጀመርኩ ፤

በ1932 ዓ.ም. በደረሰው የእሳት ቃጠሎ ምክንያት የፈሰሰው ውሃ ባስከተለው የቀለም ለውጥና በአደጋው ምክንያት የተፈጠሩት መንትያ መሥመሮች ጐልተው ይታያሉ ። እየቀረብኩ ስሄድ የምስሉ ጭጋግ የሚመስለው ጥቁር ቡና አይነት ቀለም ከጨርቁ ጋር ተመሳሰለብኝ ።

ደሙ ከአካሉ የጠቆረና ወጣ ብሎ የሾለ ነው ። ከራሱና ከክንዱ የተንጠባጠበው ደም ከእጁ ከጐኑና ከእግሮቹ ላይ ተጋግሮአል ። በብዛት ጐልተው የሚታዩት በኃይል የተመቱት ክፍሎች ናቸው ከተመታው ክፍል ምልክት ጫፍ ላይ ያበጡ የሰውነት ክፍሎች ይመስላሉ ምንአልባት በሮማውያን መግረፊያ ጫፍ ላይ እርሳስ ወይም አጥንት በታሠረበት የተመታው ይሆናል።ከከፈኑ ላይ ከሥዕሉ በግልጽ የሚነበበው ከሰብአዊ ርኅራኄ ውጭ በሆነ ጭካኔ የተሞላ ሥቃይ የደረሰበት ነው ።

ጨርቁ ጥንታዊ ወይንም በቅርብ ጊዜ የተሠራ ይሁን አይሁን ምስሉ እንዴት እንደ ታተመ ደሙ ትክክለኛ ደም ከፈኑም ዕውነተኛ ወይም ማጭበርበሪያ ይሁን አይሁን መገመት አልቻልኩም ። እንዚህንም ጥያቄዎች ለመመለስ ነው ሳይንቲስቶች የሚጥሩት ።

ከፈኑ ከሳይንስ ጋር ሲገናኝ የመጀመሪያው ጊዜ አይደለም ። ቅርሱ መጀመሪያ ጊዜ ፎቶግራፍ የተነሣው ከሰማንያ ዓመታት በፊት በ1898 ዓ.ም. ነው ። ፎቶግራፎቹ በጣም አስደናቂ የሆኑትን ብዙውን የከፈኑን ምሥጢር ገልጠውት ነበር ። ስኮንድፒያ የተባለው ፎቶግራፍ



አንሺ የመጀመሪያውን "ግላስፕሌት" (Glass plate negative) ልዩ ፊልም በሚመረምርበት ጊዜ ያየው በፎቶግራፍ ፊልም አስተጣጠብ እንደ ተለመደው ትክክለኛ ያልሆነውን ፎቶግራፍ ሳይሆን ግልጽ የሆነ ፓዘቲቭ(Positive Image) መልክ ነው ።

የሚታዩ ጥላቸው ከጨርቁ ላይ የተዟዟሩና ከሕይወታዊ ተመሳሳይነት እውነታዊነት በጣም የራቁ ናቸው በተጨማሪም ያሳዩት የነበረ ዝርዝር ከከፈኑ ላይ ታይቶ ያልታወቀውን አሁን ግን እላይ ተቃራኒ ምስል ( Negative Image ) የተገለጸውን ነው ።

ውም ተሰንዝሮበታል ዩሊስ ቸባለሪ በፈረንሳይ በጣም የተማረ ምን አልባትም በዓለም ውስጥ ተብሎ የሚነገርለት ሃምሳ ያህል የሚሆኑ ከፈኑን የሚመለከቱ መዛግብተ ሐተታ ከተመለከተ በኋላ ስሕተት ነው በማለት ሐሳቡን ገልጦአል ።

( Biologist pro-pounds vapor theory)
ባዮሎጂስቱ ቬፐር ቲኦሪ መፍትሔ እንዲያገኝ አቀረበ


ታዋቂ የሆነው ዚኦሎጂስቱ ዋይቨስ ደላግ የከፈኑን ሁኔታ ደገፈ ፤ ጳውሎስ ዮሴፍ ቢገኖን ከተባለው ወጣት ባዮሎጂስት ጋር ሁኖ በጥንቃቄ የፒያን ፎቶ


በጥንቱ የቀብር ሥነ ሥርዓት ከዘይት ጋር ይጠቀሙበት የነበረ ቅመማ ቅመም የቀብሩ ዕቃዎች በቶሎ እንዲቀበሉት አድርገዋል ሲል መላ ምት አቀረበ ። ከተሰቃየ ሰውነት የሚወጣ ጤነኛ ያልሆነ ላብ " Urea " (ዩሪያ) የተባለ ቅመም እንደሚወጣና በዚያው "Ammonia vapor" (አሞኒያ ቬፐር) እንደሚሰጥ ተረዳ ። ምክንያቱንም ሲያቀርብ ይህ ቬፐር የተነከረውን ጨርቅ ወደ ቡና አይነት እንዲለወጥ አድርጐታል ።

ሙከራ አደረገና የመልኮች ክፍል ሰጣቸው ። Vaporograph theory (የቬፐሮግራፍ ቲኦሪም ተወለደ ሁለቱ ሰዎ



*Pilgrims of science,* with white-glove care, anchored the shroud to a rotating frame designed for an exhaustive series of tests (above). Organized as the Shroud of Turin Research Project, more than thirty Americans worked nonstop for five days alongside Italian scientists. An early discovery: "Blood images, unlike body images, penetrate the shroud and are dense enough to be visible under back lighting (right). But is it blood? Biophysicist John Heller, silhouetted before minute shroud fibrils (above right), ran chemical and spectroscopic tests on fibrils and concluded, "It's hemoglobin." But he and other team members plan more tests





የሳይንስ ሊቃውንት በልዩ ልዩ ዘመናውያን መሣሪያዎች እየተረዱ በጌታ መግነዝ ላይ ምርምር ሲያደርጉ

የተቃራኒ (ነገቲቭ ምስል) ፎቶግራፍ ከመፈልሰፉ መቶዓመታት በፊት ከፈኑ ለማታለል የተዘጋጀ ነው የሚለው ሐሳብ እውነት አይመስልም ። እንዴት የመካከለኛው ዘመን አርቲስት ነጌቲቭ(ተቃራኒ) ምስል ሠራ ለምንስ ይህን መረጠ?

የቱሪን ውድ ዕቃ በአሁኑ ጊዜ በጣም አስፈላጊ ዕቃና ከፍተኛ የመወያያ ርእስ ሁኖአል ። በአሁኑ ሰዓት (ጊዜ) ከታወቁት ጸሐፊዎችና የታሪክ ሰዎች ተቃ

ግራፎች አጥንቶ መልኩም (ምስሉ) እንዴት እንደ ተሠራ በጥልቅ ተመራምሮበታል ። ቀለም ቅብ ይሆንን ? እርሱና ቢገኖን በዘይት ለማራባት ሞክረዋል በውሃ ቀለሞችም ሞክረው ነበር ነገ ርግን አንዱም ሙከራቸው አልሠራም ።

ቢገኖን እንደገና ነገሩን ለመያዝ ሌላ አይነት አቀራረብ ተጠቀመ ። ከርቤና ዋግራ ሽቱ ወፍራምና ሹል ቅጠል

ች መልኩ እንዴት እንደ ተሠራ ለማወቃቸው ዕርግጠኞች ነበሩ ።

በ1902 ዓ.ም. ደላግ ወደ ፈረንሳይ አካዳሚ ሂዶ የሙከራውን ዝርዝር ጥናት አቀረበ።በሐሳቡ ማጠቃለያ የሚገኘውን ፈተና ለመታገስ በመወሰን "የከፈኑ ሰው ክርስቶስ ነበር" ብሎ ደመ ደመ ።

የጥናቱ ተቅዋምም አጥብቆ ተቃወመው ሐሳቡንም በጽሑፍ ለማስፈር እም



www.ethiopianorthodox.org

ቢ አለው ። ክርክሩም እየተጧጧፈ ሄደ ።

ከሠላሳ ዓመታት በኋላ የታወቀው የፈረንሳይ የቀዶ ጥገና ሐኪም ዶክተር ፒረቨርቤት ከፈኑን አየና በ1931 ዓ.ም. ጊዮሴፕ ኢንሪ አማካኝነት በተነሡት ፎቶግራፎች ላይ ፍላጐት አደረበት ባር ቤት በከፈኑ ላይ ምልክቶችን አናቶሚካዊ ትክክለኝነት ለማረጋገጥ ስለፈለገ በአስከሬን መሰል ነገር ላይ ሙከራ አደረገ ። ወዲያውኑ በመዳፉ ላይ የተቸነከሩት ችንካሮች የሰውዬውን አካል መደገፍ እንደማይችሉ ተረዳ ። በሌላ በኩል የአምባር መዋያውን ወይም እጁን ችንካር መብሳት አይችልም ።


ቃል “ Cheir ” (ኤር) የሚለውን ከንድንና የአምባር መዋያን እንደሚጨምር ስለማያውቅ ይሆናል ።

ምንም እንኳ ሮማውያን በመስቀል ላይ ብዙዎችን ቢያሠቃዩም (ከ6000 የስፓርታውያን ዓመፅ በኋላ) እስከ 1968 ዓ.ም. በኢየሩሳሌምየመቃብር ቦታዎች እስከ ተገኙበትና ለብርሃን እስከ ተጋለጡበት ድረስ አንድም የአጽም ቀር አይታወቅም ነበር ።

በአንድ የአጽም ማከማቻ ቦታ ጆሀናን የተባለ ሰው አጥንት አርኪዎሎጂስቶች አግኝተው ነበር በስቅላት በሚቀጡ ሰዎች እንደሚደረገው ሁሉ ከጉል

እስከዚህ ድረስ የከፈኑ ጥናት ይካሄድ የነበረው ሙሉ በሙሉ በፎቶግራፍ ላይ ነበር ። ነገር ግን በ1969 ዓ.ም. እንደ ገናም በ1973 ዓ.ም. ኤክስፐርቶች በተለይም ኢጣልያኖች እርሱን ከፈኑን እንዲያጠኑት ተፈቅዶላቸው የመጀመሪያው ቡድን ያደረገው ጥናት ላይ ላዩን ስለነበረ አዲስ ነገር አላገኘም ነገር ግን የ1 973 ዓ.ም. ቡድን ብዙ አስደናቂ ነገሮችን አግኝቶአል ።

መልኩ (ምስሉ) ሙሉ በሙሉ ከሰው ቁጥጥር ውጭ እንደሆነ ተረድተዋል ። ያረፈውም ከክሮቹ ላይ ነው በጭራሽ ዘልቆ አልገባም በተጨማሪም ቀለም ማየት እንደማይቻል አጉልተው በሚያሳዩ መሣሪያዎችም ቢሆን ማየት እንደማይቻል ሪፖርት አድርገዋል ።



የምስሉን ኋላና ፊት የሚያሳየው የጌታ ከፈን ፡

ይህ ዕውቀት የከፈኑን ዕውነተኛነት ያጠናከረው ይመስላል ። የችንካሩ ምልክት ከከፈኑ ምስል ላይ የሚታየው ከመዳፉ ላይ ሳይሆን ነገር ግን ከአምባር መዋያው ላይ ነው ማለት ከተለመደው ከክርስቶስ ሥነ ሥቅለት ሥዕል እንደሚታየው አይደለም ። የመካከለኛው ዘመን አታላይ የራሱን ምስል መሠረት ያደረገው ከአየው ሥዕልና ወንጌሎች ላይ እንደተጻፈው የችንካሩ ቀዳዶች ባለው ነው ። ምን አልባት የግሪኩን

በቱ ታችኛው ክፍል ተሰብሮአል ። እስከ አሁንም ድረስ ከቁርጭምጭሚቱ አጥንት ላይ የመስቀል ቁራጭ የወይራ እንጨት ተጣብቃለች ቢሆንም በጣም አስፈላጊና አሳሳቢ የሆነው ከቀኝ እጁ የተቸነከረው ችንካር ግልጥ ሆኖ የተላጠና የተጐዳ ቦታ ውስጠኛ ክፍል ወደ አንባር መዋያው ቀረብ ብሎ ይታያል አርኪዎሎጂ የሕክምናውን መረጃ ስለከፈኑ የሰጠውን ትክክለኝነት አጠናክሮታል ።

<u>አዋቂው ከፓላስታይን የአበባ ብናኞች አገኘ</u>

ባለፉት ጊዜያት ተደርጐ የነበረው ጥናት ከፈኑን በቅድስት ሀገር ለማድረግ የተሞከረ ይመስላል ። ሥውር ነፍሰ ገዳዮችን በሚቹ የአሚሚት ሁኔታ መርምሮ የሚያውቅ አንድ የስዊስ ሊቅ (Cirminologist ) ክራይሚኖሎጂስት) ማክስ ፍሬይ ለቤተ ሙከራ ጥናት የሚረዳ የሚጣበቅ ነገር ከከፈኑ ላይ አጣብቆ አቧራውን እንዲወስድ ተፈቀደለት። በሚያጉላ መነጽር ረዳትነት ፍሬይ ፋኔ የአበባ ብናኞች ትንሽ የተበታተነ (የወንዴ ዘር) አካል ፤ በፍሬ ወለድ ተክሎች አማካኝነት የተገኘ ለብዙ መቶ ዓመት በማይስማሙ ጊዜያት ሳይቀር ለመኖር የሚችል አገኘ ።

የብናኙ ዘሮች የተለያዩ ናቸው ግማሽ ፀጉረ ከርዳዳ ግማሹ ደረተ ገማሳ ግማሹ የሾረና ሁለት ዝርያዎች አይመስሉም ። ስለሆነም ብዙ ተክሎች በከፍተኛ ጥንቃቄ የአበባ ብናኙን በቋሚ ማመዛዘኛ ሰብስቦ እያወዳደሩ መለያየት ይቻላል ።

ከመለያያዎቹ አይነቶች መካከል ፍሬይ እንዲጠብቀው ብዙዎቹ ተክሎች ከፈረንሳይና ከኢጣልያ አገር አገኛቸው ። በተጨማሪም ሰባቱ ከ ( Halophylic ) ሀሎፊሊክ ጨው ወዳጅ ተክሎች ከጨውማ አካባቢዎች እንደሙት ባሕርና ሌሎች



ከፓላስታይንና ከአናቶሊያ ነበሩ ። የፍሬይ ፍለጋ ከፈኑ አንድ ጊዜ በታሪክ ውስጥ ከቅድስት ሀገር እንደ ነበረ ሀሳብ ያቀርባል ።

ነገር ግን ሁሉም ሳይንቲስቶች ያለተቃውሞ ይህንን መረጃ ለመቀበል ዝግጁዎች አይደሉም ። የአበባ ዱቄት የሚዋለደው ከሩቅ ቦታ በሚመጣ ነፋስ በአዕዋፍና በተጓገሮች ነው ። ከፈኑ እንደሚታወቀው ይታይ የነበረው ለመቶ ዓመታት ያህል በተደጋጋሚ ከውጭ ያለ ምንም ከለላ ነበር ።

በደንብ የተደራጀ ፍለጋ በሁለት ቁርጥራጭ ወረቀቶችና በ1973 ዓ.ም. ከከፈኑ በተወሰዱ በዛ ባሉ ክሮች ላይ በመመርኰዝና እንደገና ዓለም አቀፍ ታዋቂ በነበረው የቴክስታይል (የጨርቃ



በጌታ የመገነዝ ጨርቅ ላይ ሳይንቲስቶች ምርምር ሲያደርጉ

ጨርቅ) ኤክስፐርት ተመራማሪ የጌኔንት ዩኒቨርሲቲ ፕሮፌሰር ጊልበርት ራይስ (የቤልጅግ ተወላጅ) ተደርጐ ነበር ።

በጥቂቱ የጥጡ ምልክቶች ያመለከቱት ወደ ቅድስት ሀገርና ጥንታዊ እንደሆነ ይመስላል ። ነገሩ ብዙ ጊዜ የበፍታ ጨርቅ ነው ። ሪያስ የመሀከለኛው ምሥራቅ አይነት የጥጥ ምልክቶች አገኘ ።

ምንም በድሮ ጊዜ የተለመደው አይነት አሠራር ልቅ አይነት ቢሆንም ክሮቹ የከረሩት በእጅ ይመስላል ። በግምት

1200 ዓ.ም. በኋላ የአውሮፓውያን ክር ይከር የነበረው በመሣሪያ ነው በመጨረሻ ክሮቹ በጥንቱ ልማድ መሠረት ከመሠራታቸው በፊት መንጣት እንዳለባቸው ይታመን ነበር ።

<u>በሦስት አቅጣጫ ማንበብ</u>

በአሜሪካን አገር በከፈኑ ላይ ሳይንሳዊ ፍላጐት የተነሣው በሁለት ወጣት የአየር ኃይል ሳይንቲስቶች በዮሐንስ ጃንክስንና ኤሪክ ጃምሸል ነው ። እስከ 1974 ዓ.ም. ጥልቅ የሆነ ጥናት በኢንሪ ፎቶግራፎች ላይ አደረጉ ። እንደ ቪግኖን የጥቁሩን ወይም እያንዳንዱ የምስሉን ክፍል ከሚሸፍነው ኃይለኛ አንሶላ ርቀቱ ከአካሉ ክፍል በቀጥታ በመጠን የተለያየ ነው ። የጥቁሩ ክፍል ለአንሶላው በጣም የቀረበ ሲሆን ብሩሁ ደግሞ ራቅ ያለ ነው ። ምስሉ በሆነው ነገር ይፈጠር ድርጊቱ የተደረገው በቀጥታ ግንኙነት ሳይሆን ራቅ ካለ ቦታ እንደሆነ ደምድመዋል ።

ሀሳባቸውን ግልጽ ለማድረግ ሥዕሎቹን የምስሉን ኃይል ለውጦ ቀጥተኛ ቅርጽ እንዲያሳይ ሆኖ በተዘጋጀና በተቀነባበረ(ቪፒ-፰ Image Analyzer) በተባለው ምስል ተንታኝ መሣሪያ በመጠቀም በተከታታይ አጠኑት በአስደናቂ ሥራቸው ከፈኑ በትክክል የተለመደ ፎቶ ግራፎች ወይም ሥዕሎች የሌላቸውን ከፈኑ ትክክለኛ ሦስት መረጃ

ያለው መሆኑን አገኙ ። በኮምፒዩተር መረጃ የምስሉን ሦስት አቅጣጫ ሞዴል ለመሥራት ችለው ነበር ይህ ሥራ በከፍተኛ ደረጃ በተሠማሩበት ሥራቸው የሠለጠኑትን ሳይንስቲቶች ሕሊና ማረከ በ1977 ዓ.ም. መጋቢት ወር አንድ የጥናት ቡድን ከአውሮፓ ከመጡ ብዙ የከከፈን ጠበብቶች ጋር በአልቡከርስ በኒው ሜክስኮ ተገናኙ ። ያ ስብሰባ ከፈኑን በሚቀጥለው ዓመት በቱሪን ከተማ ለሕዝባዊ ትርኢት ሊቀርብ በሚወጣበት ጊዜ በሳይንሣዊ መንገድ ለመሞከር ወይም ለማጥናት አቀደ ።

ወደ ቱሪን ከመመለሳቸው በፊት በአሜሪካ በአንድ ሰበካ ያገለግሉ በነበሩ ኢጣልያዊ አባት (ካህን) ጴጥሮስ ፊና ልዲና በአሜሪካ የከፈኑን እንቅስቃሴ ለረጂም ጊዜ መሪ በነበሩት አባት አዳም ጂኦተርቤያን አማካኝነት ሕጋዊ ፈቃድ ፈለጉ ። የዱሮው የኢጣልያ ንጉሥ ዳግማዊ አምባርትና የከፈኑ ሕጋዊ ባለቤት የሳቮይ ቤት የበላይ ለብዙ ዓመታት ሙከራውን ፈቅደው ነበር ከግዞት ቤቱም ከፖርቱጋል ማረጋገጫ ሰጥቷል ። የቱሪን ሊቀ ጳጳስ አንስታስዩ ባሊስትሬሮ ቅርሱን በኃላፊነት እንዲጠበቅ የተሰጠውም አረጋግጦአል ። ሳይንቲስቶቹ ለማንኛውም ጉዳት ለማያስከትል ጥናት በእጃቸው አስረከቦአቸዋል ።

ስለዚህም ነው የቱሪኑ የጥናት ፕሮጀክት ሊቋቋም የቻለው ቡድኑ ለጥናቱ ዝርዝር ዝግጅት የተለያዩ መሣሪያዎችን መሰብሰብና መርሐ ግብርን ማውጣት ጀመረ እሁድ ማታ ጥቅምት ፰ ቀን 1978 ዓ.ም. የቱሪን ትርኢት አለቀ ። የመጨረሻው ተሳላሚ (ጐብኚ) ካቴድራሉን እንደለቀቀ ናይትሮጂን ከተመላው ማስቀመጫው ወጥቶ ወደሚቀጥለው ቤተ መንግሥት ተወሰደ ። ጐብኚ የንጉሥ ቤተሰቦችን ለመቀበል ይጠቀሙበት በነበረው መልካም አዳራሽ ለአምስት ቀናት እንዲቆይ ሆነ ። ሳይንቲስቶችም (የኢጣሊያን ቡድንና የስዊ

ወደ ገጽ ፳፪ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

# ምን እንርዳዎ ?

ይህ ዓምድ አንባቢዎች ችግራቸውን የሚገልጹበት ፣ ለችግራቸው መፍትሔ የሚሰጡበት ፣ ጥያቄና መልስ የሚያቀርቡበት ስለሆነ ምን እንርዳዎ ተብሎ ተሰይሟል ።




አዘጋጅ ተስፋ ጥሩነህ

ስልክ ቍጥር 11-66-16

የፖ.ሣ.ቁ. 31-37

አዲስ አበባ


ለትንሣኤ መጽሔት ምን እንርዳዎ ዓምድ አዘጋጅ
አዲስ አበባ

ላውቀው የምፈልገው የቸገረኝ ነገር ስላለ በምን እንርዳዎ አምድ ዘርዝረህ እንድታስረዳኝ ጥያቄ አቅርቤአለሁ ፤

1ኛ/ ከቀብር መልስ ከቤት ሳይገባ ለቀስተኛው እጁን የሚታጠበው ለምንድር ነው ? ከየትስ የመጣ ባህል ነው ይኸውስ መቼ ተጀመረ ?

2ኛ/ በሐዘን ጊዜ ጥቁር ልብስ የሚለበሰው ለምንድር ነው ? ይህስ በየትና መቼ በማን ተጀመረ ? ፤

3ኛ/ በሣልስትና በ40 ወደ ቤተ ክርስቲያን እየተሄደ ይለቀሳል አሁን ግን በአዲስ አበባ ወደ ቤተ ክርስቲያን መሄዱ ቀርቶ ከቤት ይለቀሳል ። ቢሆንም በ40ና በሳልስት ማልቀስ መቼ በየት ተጀመረ ምክንያቱስ ምንድር ነው ? ከላይ ለዘረዘርኳቸው ጥያቄዎች አጥጋቢ መልስ ትሰጠኝ ዘንድ ዓምድህን በናፍቆት እጠባበቃለሁ ፤

ገብረ እግዚአብሔር ኃይሉ
ከአዲስ አበባ

አቶ ገብረ እግዚአብሔር ኃይሉ ያቀረቡት ጥያቄ ሌሎችም ሊያውቁት የሚፈልጉት ስለሆነ ይመስገናሉ ።

1ኛ/ ከቀብር መልስ ከቤት ሳይገባ ለቀስተኛው እጁን የሚታጠበው በቀብር ጊዜ በሥራ የዋለው እጅ ማለትም ከአፈር ጋር የዋለውን እጅ ታጥቦ የእገዝን ጥሬ ለመብላት ነው ይባላል ይህም መቼ እንደተጀመረ ለማወቅ ብዙ አረጋውያንን አነጋግሬ መልስ አላገኘሁም አሁንም ስለዚሁ ጉዳይ ሰፋ ባለ ሁኔታ የሚያቀርብ ካለ መልሱን በደስታ ተቀብለን በዚሁ ዓምድ ለማውጣት ዝግጁ ነን ።

በሌላ በኩልም ከቀብር መልስ እጅን መታጠብ ሞት ባለበት ቤት በሽታ ስለማይጠፋ ከዚሁ ለመጸዳዳት ነው የሚሉ አሉና ይህም እንዴት እንደሆነ የሚገልጽልን ብናገኝ እንደሰታለን ።

ስለ 2ኛው ጥያቄ በኃዘን ጊዜ ስለሚለበሰው ጥቁር ልብስ ጉዳይ ነው ። ይህ እንኳ ቀደም ሲል በኦሪት ዘመን ብዙ ጊዜ ይደረግ እንደነበረ አንዳንድ ምልክቶች ለማግኘት እንችላለን ።

ነቢያት የመከራ ወይም የኃዘን ትንቢት ሲናገሩ ጥቁር ልብስ ለብሰው ጥቁር ሻሺ ጠምጥመው ፤ ጥቁር መነሳንስ (ጭራ) ይዘው ፤ በጥቁር ፈረስ ላይ ተቀምጠው ከፉውን ትንቢት ይናገሩ እንደነበረ ይነገራል ።

ይህም በእስራኤል ዘንድ ለብዙ ጊዜ ልማድ ሆኖ ሲሠራበት እንደቆየና በሐዘን ጊዜም ጥቁር መልበስ የኃዘን ምልክት ሆኖ እንደቆየ እንረዳለን ። በኢትዮጵያም ይህው ጥቁር መልበስ ልማድ ሆኖ እንደቆየ ከመረዳታችን በቀር ሌላ ለማግኘት አልቻልንም ።

ስለ3ኛው ደግሞ በሶስተኛውና በአርባው ቀን ወደ ቤተ ክርስቲያን እየሄዱ ማልቀስ የመጣው አሁንም ከኦሪቱ ሥርዓት በእስራኤላውያን ዘንድ ነው በሳልስት ስለማልቀስ ይህንኑ ልማድ በማክበር እነማርያም መግደላዊት የፈጸሙትን ብንመለከት በቂ ማስረጃ ነው ።

ይህም በእስራኤላውያን ዘንድ አንድ ልማድ ነበረ ልማዱም ሰው በተቀበረ በ3ኛው ቀን ከተቀበረበት ቦታ ድረስ ሄዶ መቃብሩን ከፍቶ ሺቱ ማርከፍከፍ እና እዚያው ማልቀስ ነበር ። በዚህም መሠረት መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አርብ ተቀብሮ ስለነበረ ማርያም መግደላዊትና ጓደኞቿ እንደልማዱ ሺቱ ይዘው መቃብሩን ሊረጩ ሄዱ ፤ እርሱ ግን ቅዱሳት መጻሕፍት እንደተናገሩት በሶስተኛው ቀን ከሙታን ተለይቶ ተነስቶ መቃብሩን ባዶ ሆኖ ስለአገኙት እንደፈለጉት አላደረጉም ዮሐ. 20 ፤ 1 - 18 ።

በ40 ቀን ስለማልቀስም ቢሆን ብዙ ጊዜ እንዲያውም ያለዕረፍት እስከ አርባ ቀን ድረስ የሟቹ ሬሳ በሺቱ እየታሸ ይለቀስ ነበረ ኦሪ . ዘፍ. 50፣ 3፣ እንዲያውም እስከሰባ ቀንም ይለቀስ ነበር ። ዳሩ ግን ያ በኦሪቱ ጊዜ ይለቀስ የነበረው ልቅሶ ቀርቶ በዘመነ ክርስትና በለቅሶው ምትክ ጸሎተ ፍትሐት ስለተተካበት በክርስትና ሕግ አብዝቶ ማልቀስ አጥብቆ የተከለከለ ነው ። ስለዚህ ጉዳይም በተለያዩ ጊዜያት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን በተደጋጋሚ ሥርዓት የሌለው ልቅሶ እንዳይለቀስ ያስተላለፈችው ውሳኔ ተገቢ ስለሆነ አሁንም ቢሆን ደረት እየደለቁ ሙሾኛ እያስደረደሩ ማልቀስ ተገቢ ስላልሆነ የየአብያተ ክርስቲያናቱ አስተዳዳሪዎች በጥብቅ ሊቆጣጠሩ ይገባል እንላለን ።



# « ብታውቂስ ሰላምሽ ዛሬ ነበር »

ይህ ቃል የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ነው ፤ የተናገረውም ይህንን ዓለም ከበደልና ከኃጢአት ነፃ አውጥቶ ዘለዓለማዊ ደህንነት ንለማደል ሲል ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከድንግል ማርያም ተወልዶ ቀስ በቀስ ከአደጋ በኋላ በ30 ዘመኑ በዮርዳኖስ ተጠምቆ የማስተማሩን ተግባር በይፋ በጀመረበት ወቅት ነበር።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አህጉሮችን በማስመልከት አጥፊዎችን መውቀስና መገሠጽ የተለመደ ተግባሩ ነበር። « በአንጻረ በለስ ረገማ ለኃጢአት በበለስ ፤ አንጻር ኃጢአትን ረገማት እንደተባለው በሚያስተምርበት ጊዜ ቃሉን የማይቀበሉትን ሰዎች የሚወቅሳቸውና የሚዘልፋቸው በሚኖሩበት ቦታ አንጻጽሮ በመሆኑ « ወዮልሽ ኮራዜ ፤ ወዮልሽ ቤተሳይዳ፣ አንችም ቅፍረናሆም እስከ ሰማይ ከፍ ከፍ ብትይ ወደ ሲኦል ትወርጅ ዘንድ አለሽ » ብሏል ማቴ 11 21- 23 በተጨማሪም «ኢየሩሳሌም ሆይ ነቢያትን የምትገድል ወደ እርሶ የተላኩትንም የምትወግር ዶሮ ጫጩቶቿን ከክንፎችዋ በታች እንደምትሰበስብ ልጆችሽን እሰበስብ ዘንድ ስትን ጊዜ ወደድሁ » ይላል ማቴ 23 ፤ 37

ይህንና ይህንን የመሳሰሉት ሁሉ የሚያስረዱት በአህጉሮች አንጻር ሰዎቹ የሚወቀሱ መሆናቸውን ነው ክርስቶስ ኦሪትን ለመሻር አልመጣሁም ልፈጽም ነው እንጂ ባለው ቃል መሠረት የቆየውን የዕብራውያንን ባሕል በመጠበቅ በዓመት በዓመት ወደ ኢየሩሳሌም እየሄደ የፋሲካን በዓል ያከብር ነበር፣ ከበዓሉም ላይ ለተገኘው ሕዝብ ትምህርት መስጠት የተለመደ ተግባሩ ነበር፣ ከተጠመቀ በኋላ ግን በዓል ለማክበር ወደ ኢየሩሳሌም ሂዶ ለመጀመሪያ ጊዜ ነጋዴዎችን ገንዘብ መንዛሪዎችንና ለዋጮችን ከንጓዛቸውና ከነገንዘባቸው ከታላቁ ቤተ መቅደስ ቅጽረ ግቢ አስወጥቶ አባረራቸው። ከዚህ በኋላ ለሶስት ዓመት ያህል ቆይቶ እንዲሁ ደግሞ እንደገና የፋሲካን በዓል ለማክበር ሲል ኢየሩሳሌም ከተማ ላይ ተገኝቷል፣ ነገር ግን ከሦስት ዓመታት በፊት ወደ ኢየሩሳሌም ከተማ የመጣው ያለ አጀብ ብቻውን ነበር ብዙ ሕዝብ አስከትሎ ካለመምጣቱም የተነሣ በተቃዋሚዎች ፈሪሳውያን ላይ ሥጋት አላደረባቸውም ነበር።

ለመስቀል አንድ ሳምንት ሲቀረው ወደ ኢየሩሳሌም ከተማ ሲገባ ግን ሁኔታው ሁሉ ተለውጧል በፊት በኋላ በቀኝ በግራ በሽማግሌዎችና በሕፃናት ታጅቦ እየተመሰገነ መጥቷል የሕፃናቱና የሕዝቡም ዝማሬ ሆሣዕና በአርያም በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ የተመሰገነ ነው የሚል ነበር። ሰዎቹ ብቻ ሳይሆኑ ደንጊያዎችም ለዚሁ ምስጋና ተባባሪዎች በመሆን እንደ ሰው አፍ አውጥተው አመስግነዋል።

የኢየሩሳሌም ሰዎች ግን ክርስቶስ ተወልዶ በአደገበት አካባቢ እያሉ ስለ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሚያውቁት አንዳች ነገር አልነበራቸውም ፤ ከዚህም የተነሣ ኢየሱስ የዓለም መድኃኒት መሆኑን አልተቀበሉም ፤ እንዲያውም አንዳንድ ሰዎች ይህ የምትዘምሩለት ሰው ማነው ? ይልቁንስ መዝሙራችሁን ትታችሁ አርፋችሁ ተቀመጡ በማለት የሚዘምሩትን ሕዝቦች መከሯቸው ።

የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ተከታዮች ግን ዓለምን ለማዳን የመጣውን የኢየሱስ አምላክነት በሚገባ ስለተረዱት «ሆሣዕና ለዳዊት ልጅ በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ የተባረከ ነው»እያሉ መዝሙራቸውን እየመላለሱ በመዘመር ወደታላቁ ቤተ መቅደስ የሚጓዘውን ኢየሱስን ይከተሉት ነበር መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሽማግሌዎችና በሕፃናት አፍ እየተመሰገነ ከቤተ መቅደስ ቅጽረ ግቢ በደረሰ ጊዜ የከብት ነጋዴዎች ፣ገንዘብ መንዛሪዎችና ለዋጮች ኢየሱስን ለመቃወም ኃይላቸውን አስተባብረው ተነሡ፤ኢየሱስ ግን ተቃውሟቸውን ከምንም ሳይቆጥር በቤተ መቅደስ ሳለ የመጡትን በሽተኞች ሁሉ ፈውሷቸዋል ይሁን እንጂ በዚያ የነበሩት ፈሪሳውያንና የካህናት አለቆች አልተደሰቱም በኢየሱስ ላይም በይበልጥ ተናደዱ እንጂ ።

በፊተኛው ጊዜ ኢየሱስ ወደ ዚሁ ቤተ መቅደስ ብቻውን ያለ አጀብ መጥቶ ሳለ አልፈሩትም ነበር በኋላ ግን ብዙ ተከታዎች ስላሉት ካህናቱና ፈሪሳውያን ኃይሉንና ሥልጣኑን ፈሩ ኢየሱስን እንዳያስተምር ለማድረግና ተከታዮቹንም ቁጥራቸው ከቀን ወደ ቀን እየበረከተ እንዳይሄድ ለመከላከል የሚችሉበትን መንገድ በምሥጢር እየተሰበሰቡ መማከር ጀመሩ። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የፈሪሳውያንን ተቃውሞ ከምንም ሳይቆጥር የሚቀርብለትን ምሥጋና ተቀብሎ ሲያበቃ ከተከታዮቹ ጋር ከቤተ መቅደስ ወጥቶ ከኢየሩሳሌም ሁለት ማይል ያህል ርቃ ወደምትገኘው ወደ ቢታንያ ወደ ሚኖርበት ተመልሶ ሲሄድ በኢየሩሳሌም አካባቢ የሚገኙትን ሕዝቦች ሁኔታ ተመልክቶ « ኢየሩሳሌም ሆይ ሰላምሽ የሚሆንበትን ቀን ብታውቂስ ሰላምሽ ዛሬ ነበር ። ነገር ግን ደኅንነትሽ የሚደረግበትን ቀን አላወቅሽም ስለዚህ አሁንም ሰላምሽ ከዓይንሽ ተሠውሯል እያለ ለከተማይቱ አለቀሰላት » ሉቃስ 19 ፤ 41

ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም የመጣው ይህንን በኃጢአት የጠፋውን ዓለም ለማዳን ስለሆነ ልዩ ልዩ መከራን ተቀብሎ በመስቀል ላይ ሕይወቱን ስለሰው ልጆች ነፃነት የሚሠዋበትን ዕለት በትዕግሥት ይጠባበቅ ነበር። የኢየሩሳሌም ከተማ ሰላም የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስን አልቀበልም አላውቅም ብላ ገርፋ ሰቅላ ስለገደለችው ከመወቀስም ሌላ ራስም በጠላቶቿ እጅ ፈራርሳለች ።


ተከታዩ ወደ ገጽ ፲፱ ዞሯል





www.ethiopianorthodox.org

# የሴቶች ዓምድ

አዘጋጅ ብርሃን ተድላ

## ለምቀበርበት ቀን ይሆናል

«ተፈጥሮ ካደለችን ጸጋዎች አንዱ በ
ሞት መጠቃለል ነው » ሲል ሚካኤል
ሞንቴን እንደተናገረው ሁሉ የአዳም
ልጆች ሁላችን ተራችን ሲደርስ ሞተን
እንደምንቀበርእናውቃለን፡፡መቼእንደም
ንሞትና ሞተን ስንቀብር ምን እንደሚያ
ጋጥመን ስለ ራሳችን ምንም አናውቅም
እርግጥ ጥቂቶቹ መች እንደሚሞቱ ይና
ገሩ ይሆናል ግን ከዚያ በኋላ በመ
ቃብራቸው ምን እንደሚፈጸም አይናገ
ሩም ነቢያት ብዙ ተንብየዋል ይሁን እን
ጂ ስለራሳቸው አልተናገሩም ።

ስለ ሰዎች ኃጢአት እራሱን አሳልፎ
የሰጠው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን
ስለራሱ ወደፊት ምን እንደሚፈጸምበ
ት እየዞረ በሚያስተምርበት ጊዜ በምሳ
ሌ ያስተምርና ይናገር ነበር፡፡ከንግግሩም
መሃል አንዱ « ለምቀበርበት ቀን ይሆ
ናል ጠብቂው » እንዳለ በመጽሐፍ ቅዱስ
ተጽፎ እናገኘዋለን ። በመጀመሪያ ግን
ጠብቂው ስለተባለችው ሴት የሕይወት
ታሪክ እንመልከት ስሟም ማርያም መግ
ደላዊት ትባላለች ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ዓለ
ም እየተመላለሰ ሲያስተምር በነበረበት
ዘመን ተከታዮቹ የነበሩት የደቀ መዛሙ
ርቱና እንዲሁም የሠላሳ ስድስቱን ቅዱ
ሳት አንስት የሕይወት ታሪክ አጠቃሎ
የሚናገረው ዜና አይሁድ የተባለው የታ
ሪክ መጽሐፍ ስለ ማርያም መግደላዊት
የመጀመሪያ ሕይወቷና ኑሮዋም በም
ን ዓይነት መንገድ ይመራ እንደነበር ሲያ
ብራራ ፦

ማርያም መግደላዊት መግደሉን በተ
ባለው ቀበሌ ተወልዳ ያደገች ስትሆን
መግደላዊት እየተባለች ትጠራ እንደነ
በር ይገልጻል፡፡ ኑሮዋን ባልተስተካከለ
መንገድ የምታካሂድ ሕገ ወጥ ነበረች
እርሷም የምትፈጽመው የዝሙት ድር
ጊት ኃጢአት መሆኑን እያወቀች ታደር
ገው ነበር እንጂ ባለማወቅ ትፈጽመው
አልነበረም ። ይህንን መሳይ መጥፎ ተግ
ባር ትፈጽም በነበረችበት ወቅት በነበ
ረው ህብረተሰብ ዘንድ የተጠላች ነበረች፡፡
ከፍ ያለ ገንዘብም በአሰበ ደነስ /ዝሙት
ስለሰበሰበች ከበርቴ እስከመባል ደርሳ
ነበር፡፡ በተጨማሪም እርሷ በነበረችበት
ዘመን ይኖሩ የነበሩት መምህራን አታ
መንዝር ሲል ሙሴ የጻፈውን ሕግ የሻረ
ሕይወት የለውም ለኃጢአቱም ስርየት
አይገኝለትም ስለ ኃጢአት ይቅርታ ማግ
ኘቱ ቀርቶ እንዲያውም በድንጋይ ተወ
ግሮ ይሞታል የሚለውን ወደ ቀቢፀ ተስ
ፋ የሚያደርሰውን የእነርሱን ትምህርት
በማዳመጥዋ ተስፋ ከመቁረጥዋ የተነሣ
ከመጥፎ ተግባሯ ለመመለስ ምኞት አል
ነበራትም በእንዲህ ያለው ያልተስተካ
ከለ ኑሮ ተይዛ ስትባክንና ጥቅጥቅ ባለ
ጨለማ ውስጥ ተቀምጣ ሳለ አይሁድ እ
ንደ ልማዳቸው እርሷን በምትመስለው
ሴት ላይ ክስ መስርተው ወደ ጌታችን
ኢየሱስ ክርስቶስ አቀረቧት ም
ንም እንኳን እነርሱ ሴቲቱን ወንጅለው
ቢያቀርቧትም የሰውን ልማቱን እንጂ
ጥፋቱን የማይወድ ጌታችን ኢየሱስ ክ
ርስቶስ ኃጢአቷን ይቅር ብሎ በነፃ እንዳ
ሰናበታትና ተከሳሽዋ በምህረት መለቀ
ቋ መልካም የምሥራች ሆኖ በእስራ
ኤል አውራጃ ሁሉ እንደተዳረሰ መጽሐ
ፉ ይገልጻል በዚህንም ጊዜም በሥጋብቻ
ሳይሆን በመንፈስ የታመሙ ሁሉ ወደክ
ርስቶስ እየመጡ ይፈወሱ ጀመር ከዚህ
ም የተነሳ ኃጢአቷን የምታስወግድበት
መንገድ ተስፋ በማጣት ቆርጣ የነበረች
ው መግደላዊትዋ ሴት ይህን መልካም
ዜና በመስማቷ የሀሊና ዕረፍት አጣች
መንፈሷም ያለልክ ታወከ እራሷን ታስ
መረምር ዘንድ ወደ ክርስቶስ ለመሄድ
አሰበች ስለቷን ለእግዚአብሔር ብትሰጥ
ይቅርታ እንደምታገኝ ሙሉ እምነት አ
ደረገች ከዚህ በኋላ ያላትን ጌጥ ሁሉ ሸ
ጠችና በዚያም ጥሩ ሽቶ በ300ዲናር አ
ንድ ብልቃጥ ገዝታ ወደ ኢየሱስ
ሄደች ሲል ሽቱ ገዝታ ወደ ክርስቶስ እን
ደ ወሰደች ወንጌላዊው ዮሐንስ ጽፎአል።
ከፋሲካም በፊት በስድስተኛው ቀን
ኢየሱስ ከሙታን ያስነሣው አልዓዛር
ወደነበረበት ወደ ቢታንያ መጣ ፡፡በዚ
ያም እራት አደረጉለት ማርታም ታገለ
ግል ነበር፡፡አልዓዛር ግን ከእርሱ ጋርከ
ተቀመጡት አንዱ ነበረ፡፡ማርያምም ዋ
ጋው እጅግ የከበረ የጥሩ ናርዶስ ሽቱን
ጥር ወስዳ የኢየሱስን እግር ቀባች በጠ
ጉርዋም እግሩን አበሰች ቤቱም ከናርዶስ
ሽቱ መላ፡፡ ነገር ግን ከደቀ መዛምርቱ አ
ንዱ አሳልፎ ሊሰጠው ያለው የስምዖን
ልጅየአስቆሮቱይሁዳይህሽቱ ለሦስት
መቶዲናር ተሸጦለድሆችያልተሰጠስለ
ምንነው?አለ ይህንም የተናገረ ሌባ ስለነ
በረ ነውእንጂ ለድሆች ተገድዶላቸው
አይደለም፡፡ ከረጢትም ይዞ በውስጡ ከ
ሚገባው ይወስድ ስለነበር ነው፡፡ኢየሱ
ስም ለምቀበርበት ቀን እንድትጠብቀ
ው ተውአውት ድሆችስ ሁልጊዜ ከእ
ናንተ ጋር ይኖራሉና እኔ ግን ሁልጊዜ
ከእናንተ ጋር አልኖርም አለ ። የዮሐን
ስ ወንጌልም .12፡1-8



እንደተጠቀሰው ሴቲቱ ከህፃንነቷ ጀ
ምራ የሠራችውን ስህተት ሁሉ አንድ
ባንድ ዘርዝራ ተናዘዘች ከዚህ በኋላ ጌታ
ችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግመኛ እንዳት
በድልና ወደ ቀድሞ ተግባሯም እንዳት
መለስ መክሮ ኃጢአቷን አስተሰረየላት
ከእግዚአብሔር አምልኮትና ከህ
ብረተሰቡ አንድነት ለይቷት የነበ
ረውን ኃጢአት አስወገደላት ከሰላሳ
ስድስቱ ቅዱሳት አንስት መካከል አንደ
ኛዋ ሁና እንድትቆጠር ፈቀደላት ሐዋ
ርያትም እየተዘዋወሩ በሚያስተምሩበት
ጊዜ በዓለም አካባቢ ሁሉ ስለ ሠራችው
ደግነት ስሟ እንዲጠራ ተናገረ ።

እርሷም ይህን እድል ከክርስቶስ በማ
ግኘቷ እየተደሰተች ገንዘቧን ያላትን ሁሉ
ለችግረኞች ሰጥታ እርሱን ተከተለች ።

እንግዲህ የዚችን ሴት ታሪክ ከመጀ
መሪያ እስከ መጨረሻ ድረስ ከላይ እ
ንደተዘረዘረው ተመልክተናል ይህች ሴት
በሰውም ዘንድ የተጠላች ነገሯም የማይ
ደመጥ ነበረች ይሁን እንጂ ኃጢአተኛ
መሆኗን አምና ከኢየሱስ ፊት በመመስ
ከሯ ሕይወትዋን አዳነች ለሌሎችም ኃ
ጢአተኞች ንስሐ እንዲገቡ ጥሩ ምሳ
ሌሆና ተገኘች ።

ነቢዩ ሰሎሞን ከመልካም ሽቱ መልካ
ም ስም ይበልጣል ሲል በምሳሌው እንደ
ተናገረደታወሳል ይህንን አነጋገርየተገ
ነዘበችው ይህች ሴት ከመልካም
ሽቶ ይልቅ መልካም ስም እንደሚበልጥ
አወቀች መልካም ሽቱ ለክርስቶስ አበር
ክታ መልካም ስም ለራሷ ወሰደች ነገ
ር ግን ለጌታዋ ያቀረበችው ሽቱ
ብቻ አልነበረም የኃዘን መግለ
ጫም የሆነውን እንባዋን ጭምር ከእ
ግሩ ሥር በብዛት አፈሰሰች በዚህ ጊዜ እው
ነተኛ የሆነው እንባዋ ከልብ ካቀረበችው
ገጸ በረከት ጋር የእግዚአብሔር ፀጋ ስለ
ተጨመረበት በኃጢአት ተጋርዶ የነበ
ረው መንፈሳዊ አይኗ ተከፈተላትና ክር
ስቶስን ለማየት በቃች በርሱም ጥላሥር
ተጠልላ ለመኖር ቻለች ።

በሽታውን ለደበቀ መድኃኒት አይገ
ኝለትም እንደሚባለው ኃጢአቱን የሠ
ወረ ራሱን ለካህን ያላስመረመረም ደኅ
ንነቱን ሊያገኝ አይችልም ምክንያቱም
ቃሉ ራስህን ለካህን አስመርምር ይላል
ና የመግደላዊትዋም ሴት ራሷን ለክር
ስቶስ ስላስመረመረች ፍጹም ድህነትን
አገኘች ።

ንስሐ ዘማዊውን እንደ ድንግል ኃጢ
አተኛውን እንደ ጻድቅ እንደሚያደርግ
ከመግደላዊቷ ሴት እንማራለን በንጹሕ
ህሊና በትሁት ልቡና ሆኖ በዕንባ መታ
ጠብ ንጹሕ ማድረጉን ከላይ በተገለጸው
ፍሬ ነገር ልንረዳ እንችላለን ያደፈ
ውን ልብስ ውኃ እንደሚያነፃው ንስሐ
ም የጎሰቆለውንና በኃጢአት ያደፈውን
አካል እንደሚያነፃ ከትምህርት የተረዳ
ን ይመስለኛል ። እንደዚህች ሴት ክር
ስቶስን በሙሉ እምነት ብንከተለው
የሥጋዊውም ሆነ የመንፈሳዊው ሕይ
ወታችን እንዲስተካከል ያደርገዋል
ልባችንን ከፍተን በእምነት ብንለም
ነው በውነቱ የሚያረካና የሚያስደስ
ት የዘላለም ሕይወት ይሰጠናል ።

ማርያም መግደላዊት ለክርስቶስ ያመ
ጣችው ሽቶ ለመቃብሩ እንዲሆን
እንድትጠብቀው በተናገራት መሠ
ረት ከሞተ በኋላ በሦስተኛው ቀን ወደ
መቃብሩ ትቀባው ዘንድ ሽቱ ይዛ እንደ
ሄደችና ተነሥቶ እንደቆያት በመጨረ
ሻም ስትፈልገው ለእርሷ ተገልጾ ሄደሽ
ለደቀመዛሙርቴ መነሳቴን ንገሪ ተብላ
የታዘዘችው የመጀመሪያይቱ ሴት መሆ
ኗን እንዘንጋ ። ይህች ሴት ወደ ሕይወት
የሚወስደው መንገድ የትኛው መሆኑን
ስላላወቀች ለመጀመሪያ ጊዜ ሁሉም ነ
ገር የተዘበራረቀና ድንግዝግዝ ያለ ሆኖ
ባት እንደነበር ከታሪኩ ለመረዳት እን
ችላለን ።
ግን በፍጹም እምነት ወደ ጌታ በመቅረቧ
እውነተኛውን የሕይወት መንገድ እንዳ
ገኘች ተረድተናል።

ስለዚህ ኃጢአት የማታለል ኃይል ስ
ላለው የሚያልፍ ቀን የማያልፍ መጥፎ
ስም የሚሰጥ መሆኑን ተገነዘብን እንደ
ሴትየዋ ጥሩ ስም ለማግኘት መልካም
ሥራ እንሥራ ልብንና የልብን ሃሳብ ጠ
ልቆ ለሚመረምር እግዚአብሔር በእው
ነት ልባችንን እናስረክበው ምክንያቱ
ም ቃሉ ልብህን ስጠኝ በማለት ይጠይ
ቃልና ።

## ሳይንስ የከፈተን : .......

ከገጽ ፲ የዞረ

ለ) ኤክስፐርቶችን ጠበብቶችን እንዲ
ሁም አሜሪካውያንን በማጠቃለል ሙከ
ራቸውን እያካሄዱ በተወሰኑላቸው ሰዓ
ት ምርመራቸውን እንዲያከናውኑ ሆነ።

አንድ ትልቅ ኃይል ያለ ጠረጴዛ የበ
ፍታውን ጨርቅ በማግኔትና በማያያዣ
ለመያዝ የሚችል ተሠርቶ ነበር ። ከፈኑ
በሚነጠልበት ጊዜ ሳይንቲስቶች ምንም
እንኳ በዕድሜ ብዛት የወየበና የታጠፈ
ብዙ እጥፋት እንዳለው መረጃ ቢያሳ
ይም በደንብ የተጠበቀና በአስደናቂ
ሁኔታ ያገኙት መሆኑን አስተዋሉ ።

ምንአልባት ከዚህ በፊት በኪነ ጥበብ
መንገድ ወይም በአርኪኦሎጂ እንደ
ዚህ አድካሚ ጥናት ተደርጐ አያውቅም
ሳይንቲስቶቹ ቅርሱን በአልትራቫዮሌት
ጨረር ( Ultraviolet radiation ) በኤ
ክስሬይ ረዳትነት በመበተን ጨረሩን
ተመለከቱ የምስሉን የደሙንና የበስተ
ኋላውን ጨረር ወይም በኤሌክትሮ
ማግኔት ስፔክትረም (Electromagnetic
Spectrum) አቋርጦ በሰፈው የሚያ
ልፈውን ኃይል ልዩነቶች ለኩ የከፈኑን
ኬሚካል (የንጥረ ነገር) የተሠራበትን
በኢን ፍራርድ ( Infrared ) በማ
ታይ ብርሃን በአልትራቫዮሌትና በኤክስ
ሬይ አማካኝነት ፈለጉ ።

የኤክስሬይ ብርሃን በደም ውስጥ ያለ
ውን ብረትና ፓታሺየም ወይም ብዙ
ጊዜ በቀለሞች ውስጥ የሚገኘውን
ነጥብ የሚያህለውን ከባድ ብረታ ብረት
ፈልጎ ማግኘት ይችላል ።

ሌሎች ጠበብት የተልባ እግሩን ጨር
ቅ በዝርዝር በተለያየ (ፎቭ ሌንግዝ)
የርግብግቢት ርዝመት በመጠቀም ወደ
500 ፎቶግራፍ አነሡ ። ጥቃቅኑን ክፍ
ል አጉልቶ በሚያሳይ መንገድ በመጠ
ቀም በመመርመር ፎቶ ማይክሮግራፍ
ሌሎችም ለትንታኔ የሚረዱ ነገሮችን

ወደ ገጽ ፲፮ የዞረ



www.ethiopianorthodox.org

# የሃይማኖት ዐምድ

> «ዓለሞች ሁሉ በእግዚአብሔር ቃል እንደ ተዘጋጁ ፡ ስለዚህም የሚታየው ነገር ከሚታዩት እንዳልሆነ በእምነት እናስተውላለን» (ዕብ. ፲፩፥፫) ።

## ምስጢረ ንስሐ

(ከቁጥር 42 የቀጠለ

ምሥጢረ ንስሐ የሚሰጠው ጥቅም ያደፈ ሰውነት ወይም ልብስም ሆነ የቤት ቆሳቁስ በውኃ ታጥቦ እንደሚነፃ እንደሚፀዳ እና እንደሚታደስ በኃጢአት የዛገና ያረጀ ሰውነትም የሚነፃ የሚጠራና የሚታደሰው በንስሐ ነው።በንስሐ መወለድ ማለት በየጊዜው ራስን ለእግዚአብሔር በማስገዛት ምሕረትን የኃጢአት ይቅርታን በመቀበል አዲስ እንደተወለዱ ሕፃናት የእግዚአብሔር ልጅነትን በመንፈስ ቅዱስ ማግኘት ማለት ነው።

በአንፃሩ ንስሐ አለመግባት ማለት የሠሩትን ኃጢአት በማሰብ በመፀፀትና በማዘን ይቅርታን ለማግኘት ወደ እግዚአብሔር በመቅረብ ፈንታ አስረዝሞ የመራቅና ከእግዚአብሔር ጸጋ የመኮብለል ምልክት ነው ። በተለይም የአዋቂ አጥፊዎች የሆኑ ማለት ራሳቸውን ና ሌላውንም ከስሕተት መጠበቅ የሚያስችል በቂ ትምህርት እያላቸው በኃጢአት ባሕር በመስጠም ራሳቸውን የልዩ ልዩ መጥፎ ልማድ ተገዥ በማድረግ በስካርና ምንዝር ወዘተ.የተበላሸ ሕይወት የሚመሩ አንዳንድ አማኞች ለዚህ ዓይነቱ ድርጊት የተጋለጡ ናቸው።ስለዚህም ክርስቶስ ስለፈሪሳውያን ሲናገር «ዕውሮች ማለት የማታውቁ ብትሆኑማ ኖሮ ኃጢአት ባልሆነባችሁም ነበር አሁን ግን እናያለን እናውቃለን ትላላችሁ ነገር ግን ኃጢአታችሁ በናንተ ላይ ጸንቶ ይኖራል » አለ ዮሐ. ፱ ፡ 41 ሐዋርያ ጳውሎስም ወደ ሮሜ ሰዎች በላከው መልእክቱ «ሌላውን የምታስተምር አንተ በመጀመሪያ ራስህን ማስተማር አይገባህምን ? አትስረቁ እያልክ ታስተምራለህ አንተ ግን ስትሠርቅ ትገኛለህ። ስለዚህም በአንተ ሰበብ የእግዚአብሔር ስም ይሰደባል በማለት የአዋቂ አጥፊዎቹን በንስሐ ለእግዚአብሔር አለመገዛት በግልጥ ጠቁሟል ሮሜ 2:21 - 24

ከምዕመናንም ወገን አንዳንዶቹ በዚህ ዓለም ስለሚሠሩት ታላላቅ በደል ምንም ሳያስቡ ቀላል የሆኑ የኃጢአት ሥራዎችን ብቻ ይናዘዛሉ ። ይህም ራስን ከእግዚአብሔር የመደበቅ ምልክት ነው። ነገር ግን ምንም ዓይነት ፍጥረት ከእግዚአብሔር ዓይኖች ተሰውሮ መኖር ስለማይችል ሁለንተናቸው የተጋለጠ መሆኑን ሊረዱት ይገባል ።

በመሠረቱ ለአማኞች የሚሰጥ የንስሐ ቅጣት ከኃጢአት ወደ ጽድቅ የሚመለሱበት ዘዴ ማስተማሪያ እንጂ እስኪማረሩ ድረስ ሕይወታቸውን የሚያስጨንቅ መሆን የለበትም በተለይም ይህ የጾም ዓርባ ኩዳዴ መዋዕለ ጾም ራሱ ሰውና እግዚአብሔር የሚቀራረቡበት የጸሎትና የንስሐ ጊዜ በመሆኑ ራስን ለእግዚአብሔር በማስገዛት ሕይወትን በቅዱስ መጽሐፍ ቃል በማደስ ክርስቲያናዊ ማስተካከያ ጊዜ ነው።

አበው ሲመስሉ አንዲት ሸክላ ሠሪ የሠራችው ጋንም ሆነ ማድጋ ስንጥቅ ወይም ነቅዕብታይበት ከስክሳ እንደገና በውሃ አርሳ እንደገና ሠርታ በእሳት ስትተኩሰው ልክ ይመጣል። አፈሩ ሳይለወጥ ሥራው ብቻ እንደገና የመታደስን ትርጽና ይዘት ይሰጠዋል ። ንስሐም ልክ እንደዚሁ ነው። ብዙ ጊዜ ባለማወቅ አንዳንድ ጊዜም አውቀው በድፍረት በሠሩት ኃጢአት ተፀፅተው ወደ እግዚአብሔር በመመለስ ራሳቸውን ለጽድቅ የሚያስገዙ ሁሉ የደህንነት በር ተዘግቶባቸው አያውቅም ።

ሆኖም ዕድሜ ለንስሐ ሰጠን በማለት ሆን ብለው አበክረው ኃጢአት በመሥራት ወይም በእልከኝነት ፀንተው ለሚኖሩ የእግዚአብሔር ልጅ እንደገና ሰው በመሆን ሥጋ ለብሶ ስለነርሱ ኃጢአት ወደ ቀራንዮ መስቀል አይጓዝም።ከዚህም የተነሣ እልከኞችን ለማዳን ሲባል የተለየ የንስሐ ዘመን ሊሰጣቸው አይችልም እንደዚህ ያሉት እልከኞች የእግዚአብሔርን ልጅ በማሳፈር የዳኑበትን ቅዱስ ደም እንዳሳደፉት ይቆጠራል በማለት ሐዋርያው ጳውሎስ ዕቅጩን ተናግሮዋል ።

ስለዚህ ንስሐ ለመግባት ነገ ዛሬ ማለት ጊዜ ማማረጥ ተገቢ አይደለም ። የንስሐ ዘመን ስጠኝ ማለት ኃጢአት የምሠራበትን ዘመን አስረዝምልኝ እንደማለት ይቆጠራል ። እግዚአብሔር ደግሞ የሰው ልጆች የሚድኑበትን እንጂ በበደል ላይ በደል ሠርተው የሚጎዱበትን እንደማይፈልግ የሚከተሉትን ጥቅሶች አንብቦ መረዳት ይጠቅማል ሕዝ 18:27 - 29

መረዳት ይጠቅማል ሕዝ.18 ፡ 27 - 29 ምሳ. 28 ፡ 13 ሉቃ 13 ፡ 5 ራእ. 2 ፡ 5

ቄስ መክብብ አጥናው

> **ብታውቂስ .......**
>
> ከገጽ ፲፩ የዞረ

አሁንም ቢሆን ሰላማቸውን ኢየሱስ ክርስቶስን የማይቀበሉና የማያውቁ ወገኖች ቢኖሩ ራሳቸው ከመጎዳታቸውም ሌላ ለሀገራቸውም የጥፋት ምክንያት ስለሚሆኑ አስቀድመው ክርስቶስን ለመቀበል መዘጋጀት አለባቸው ።

ሐዋርያው ጳውሎስ « በተወደደ ሰዓት ሰማውህ በመዳንም ቀን ረዳውህ » ይልና «እነሆ የተወደደ ሰዓት አሁን ነው የመዳንም ቀን አሁን ነው»ሲል ተናግሯል 2ኛ ቆሮንቶስ 6፡2-3ሁላችንም ክርስቶስን በምስጋና ለመቀበል መንፈሳዊ ዝግጅት ማድረግ ይገባናል የመዳናችን ሰዓትና ጊዜ አሁን ቀርቧልና ።

ቁ. ልሣነ ወርቅ በዛብህ

—— // ——



# ሦስቱ መስቀሎች በጎልጎታ

በቀድሞ ዘመን ይኖር የነበረው ሕዝብ መስቀልን በምን ሁኔታ ያየው ነበር?ምንስ ትርጉም ሰጥቶ በምን አይነት ተግባር ያውለው ነበር? የሚለውን በመጀመሪያ እንመርምር መስቀል አጥፊው ወገን በጭካኔ እንዲሰቃይበት ከሕዝብ የተዘጋጀ የቅጣት መሳሪያ ነበር።ትርጓሜውንም ስቃይ ፤ ውርደት ፤መከራ የሚፈፀምበት የቅጣት ግንድ ብለው ይተረጉሙታል።ይህም መስቀል በተግባር ላይ መዋል የጀመረው ከክርስቶስ ልደት ቀደም ብሎ ወደ ሁለት ሺ አመተ ዓለም ባቢሎናውያን ግሪኮች፣ኋላም ሮማውያን አጥፊዎችንና ወንበዴዎችን በጭካኔ የሚቀጡበት የቅጣት መሳሪያ ሆኖ ቆይቶአል ።

ይኸውም መስቀል ለመጀመሪያ ጊዜ ሲዘጋጅ አጣና መሰል ሆኖ እንደ ግንድ ነበር። እየዋለ እያደረ ግን ቅርጹ እንደ « ተ » ይሆን ጀመር እንዲሰቀልም የተፈረደበት ወንጀለኛ መጀመሪያ ይገረፋል ቀጥሎም የሚሰቀልበትን መስቀል እራሱ ተሸክሞ በተሰበሰበው ሕዝብ ፊት ያልፋል ከሚሰቀልበትም ስፍራ ሲደርስ ልብሱን ይገፈፍና እራቁቱን ይሆናል ሁለት እጆቹና እግሮቹ በምስማር ይቸነከራሉ ሊሰቀልበት ተሸክሞት ያመጣውን መስቀል ተክለው ያቆሙና በዚያ ላይ ይሰቅሉታል።

ይህንን የቆየ አጉል ባሕል መሠረት በማድረግ የዛሬ ሁለት ሺህ ዓመት አቅራቢያ አይሁድ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ን በመጀመሪያ በጲላጦስ ፍርድ ገረፉት ቀጥለውም የሚሰቀልበትን መስቀል አሸክመው ልዩ ልዩ ግፍና መከራ እየፈጸሙ ወደሚሰቀልበት ቦታ ወሰዱት በተጨማሪም የስቅላት ሞት የተፈረደባቸው ሁለት ወንበዴዎች የሚሰቀሉበትን መስቀል ተሸክመው ወደሚሰቀሉበት ሥፍራ ይጓዙ ነበር።

ይኸውም ሥፍራ በቀድሞ ዘመን የእስራኤል ዋና ከተማ በነበረው በኢየሩሳሌም ግንብ አጠገብ ጎልጎታ ተብሎ የሚጠራ አነስተኛ ኮረብታነው ። ይህም ሥፍራ «የራስ ቅል » በመባል የተለየ ስም እንዳለው በዮሐንስ ወንጌል በምዕራፍ 19 ቁ 17 ተጠቅሶአል በዕብራይስጥ ጎልጎታ ሲባል በግእዝም ቀራንዮ ይባላል ፡

ስለዚህ አንድ መንፈሳዊ ደራሲ «የአበው ተስፋ በማርያም ድንግል ተፈፀመ መድኃኒት መስቀልም በቀራንዮ ተተከለ »ሲል ተናግሮአል።ይህም ቀራንዮናጎልጎታ አንድ መሆናቸውን ያመለክታል ሊቃውንቱም በትርጓሜአቸው ሲያትቱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበት መስቀል የቆመው አዳም በተቀበረበት ቦታ ላይ ስለሆነ የራስ ቅል ተብሎ አል ይላሉ ።

ከላይ በአርእስቱ የተጠቀሱት ሦስቱ መስቀሎች ዓርብ ጠዋት ወደ ረፋዱ ላይ በጎልጎታ ላይ ተተክለው ቆመው አላፊ አግዳሚው ይመለከታቸው ጀመር እነዚህ መስቀሎች የቆሙበት ዋና አላማ ለቅጣት ሲሆን ሦስት ሰዎች ተሰቅለውባቸው ነበር በመካከል የተሰቀለው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲሆን በቀኝና በግራ የተሰቀሉት ሁለቱ ግን ነፍሰ ገዳዮች ነበሩ በየእራስጌአቸውም የሰሩትን ወንጀል የሚገልጽ ደብዳቤ ተሰቅሎ ይታይ ነበር።ሁለቱ ወንበዴዎች በየጊዜው የሰሩትን ወንጀልና የገደሉትን የሰው ዝርዝር ሲገልጽ ስለጌታችን ኢየሱስክርስቶስ በእብራይስጥና በሮማይስጥ የተጻፈው «ኢየሱስ ናዝራዊ ንጉሠ አይሁድ» ይልና በተጨማሪም «ሰንበትን ሽሮ በሽተኞችን ፈውሶአል እራሱንም የእግዚአብሔር ልጅ አድርጎአል» የሚል ነበር። ይህንም ጽሑፍ የሚያውቀው እያነበበ ፤ የማያውቀውም እያስነበበ በኢየሱስ ላይ የስድብ ውርጅብኝ ያወርዱበት ነበር። ግማሹም እራሱን እየነቀነቀ ሲዝት የተረፈውም ይስቅበትና ይቀልድበት ነበር።

እንዲያውም አብረውት የተሰቀሉት ወንበዴዎች እንኳን ሳይቀሩ እንደ ሕዝቡ ያፌዙበት ጀመር ። ሰዓት እየገፋ ሲሄድ መከራው በዚያው ልክ እየበረታ መሄዱን ቀጠለ።

ከሁለቱ ሽፍቶች በቀኝ በኩል የተሰቀለው ወንበዴ እራሱን ቀና አድርጎ በመሐከላቸው ወደ ተሰቀለው ወደ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተመለከተ ያ በመካከላቸው የተሰቀለው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «አባት ሆይ ይቅር በላቸው የሚያደርጉት አያውቁምና » እያለ ለጠላቶቹ ሲጸልይ ሰምቶ ወንበዴው ተገረመ ።

አንድ የሞት ፍርድ የተፈረደበት ሰው ሕይወቱን አሳልፎ እየሰጠ ለገዳዮቹ ሲጸልይ መስማት በእርግጥ የሚያስገርም ነበር ምንም እንኳን የተሰቀሉት ሁለት ሰዎች ፤ ነፍስን በመግደልና የሰው ሐብት በመዝረፍ የኖሩ ሽፍቶች ቢሆኑም በዚያ የተሰበሰበው ሕዝብ ስድብ ቀልድና ፌዝ ኽት በእነርሱ ላይ ሳይሆን በመሐከላቸው በተሰቀለው በክርስቶስ ላይ መሆኑ ሌላ የሚያስገርም ነገር ነበር።

ሌላም የሚያስደንቅ ነገር አለ ይኸውም የኢየሱስ ቅድስናው ትዕግስቱና ጸሎቱ የሽፍታውን ልብ ስለነካው አብሮት ለተሰቀለው ጓደኛው እንዲህ አለ « እኛስ በሥራችን ሥቃያችን እንቀበላለን ይህ ሰው ግን ምንም ለሞት የሚያደርሰው ስሕተት አላደረገም » ካለ በኋላ ፊቱን ወደ ኢየሱስ መልሶ የፈጸመውን በደል አስቦ ኃጢአቱንም እንደሚያስተሥርይለት አመነ ።

የተሰቀለውን ኢየሱስን ማየት በርግጥም ሕይወትን ይሰጣል ያ የጸለየው ኢየሱስ እንደሆነ ተገነዘበ ወዲያው «ጌታ ሆይ በመንግሥትህ ስትመጣ እኔን አስበኝ » ሲል ጸለየ ይህንን ያለው ኢየሱስ ጌታ መሆኑንና መንግሥትም እንዳለው መንፈስ ስለገለጸለት ነው በዚያ ጊዜ በቀኝ በኩል የተሰቀለው ወንበዴ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን የጠየቀው በመጣ ጊዜ በመንግሥቱ እንዲያስበው ብቻ ነበር ኃጢአተኞችን በንስሐ ተቀባይ የሆነው ስለኃጢአተኞች የተሰቀለው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ወዲያውኑ ከጠየቀው የበለጠ

ወደ ገጽ ፳፱ የዞረ



www.ethiopianorthodox.org

# በራሱ ሥልጣን ተነሣ

ከሞት የተነሡ የብዙ ሰዎች ታሪክ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ይገኛል። ለምሳሌ ነቢዩ ኤልያስና ኤልሣዕም በጸሎታቸው እግዚአብሔርን ጠይቀው በእግዚአብሔር ኃይልና ሥልጣን ከሞት እንዲነሱ ያደረጓቸው ሰዎች ታሪክ በብሉይ ኪዳን የሚገኝ ሲሆን በሐዲስ ኪዳንም እነ ዓልዓዛርና የመሳሰሉት ሁሉ በምሳሌነት ሊጠቀሱ ይችላሉ ።

የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ግን ከነዚያ ሁሉ ፈጽሞ የተለየ ነው ። ምክንያቱም እነዚያ የተነሡት በነቢያት ጸሎትና አማላጅነት በእግዚአብሔር ቸርነት እንጂ በራሳቸው ሥልጣንና መብት አልነበረም ፤ ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ማንም ሳይጸልይለት የማንም ኃይልና እርዳታ ሳይታከልለት በለበሰው ሥጋ ፍጹም ሰው ሲሆን በእውነተኛ ተዋሕዶ ፍጹም አምላክ እንደመሆኑ መጠን ለሰው ልጆች መብትና ነፃነት ሲል በራሱ ፈቃድ ሞቶ ሦስት ቀን በመቃብር ውስጥ ከቆየ በኋላ የሞትን መሣሪያ በጥሶ ፤ ሙስና መቃብርን አጥፍቶ መግነዝ ፍቱልኝ ድንጋይ ፈንቅሉልኝ ሳይል በገዛ ራሱ ሥልጣንና መብት በራሱ ኃይል በታላቅ ክብርና ግርማ በሦስተኛው ቀን ተነሥቶ ፍጹም አምላክነቱን አስመስክሯል ። "ክርስቶስ ተንሥአ እሙታን በዓቢይ ኃይል ሥልጣን ፤ ክርስቶስ በታላቅ ኃይልና ሥልጣን ከሙታን ተለይቶ ተነሣ" እ ያሉ ካህናት በየዓመቱ በትንሣኤ ዕለት የሚሰብኩትና የሚያውጁት ስለዚህ ነው ። አስቀድሞም "ሞት ሆይ መውጊያህ የታለ? ሲኦል ሆይ ድል መንሣትህ የታለ?" ተብሎ በትንቢት የተጠየቀው ጥያቄም በጌታችን ትንሣኤ ዕለት በርግጥ መልስ የማይገኝለት ከባድ ጥያቄ መሆኑ ተረጋግጧል ።

ስለ ክርስቶስ ትንሣኤ በነቢያት የተነገረው ትንቢት እጅግ በርከት ያለ ቢሆንም ጥቂቶቹን ለማስታወስ እንሞክራለን ።

። ክርስቶስ ከመወለዱ ከ1.000 ዓመት በፊት የነበረው ዳዊት "ወተንሥአ እግዚአብሔር ከመ ዘንቃህ እምንዋም" እግዚአብሔር ከእንቅልፉ እንደሚነቃ ሰው ከሞት ተነሣ ሲል እግዚአብሔር ወልድ በሥጋ ሞቶ በራሱ ሥልጣንና ኃይል እንደሚነሣ ተናግሮ ነበረ፡ ይህ ልበ አምላክ ተብሎ የሚነገርለት ነቢዩ ዳዊት ስለ ክርስቶስ ትንሣኤ የተበየው ይህን ብቻ አልነበረም ። "ይእዜ እትነሣእ ይቤ እግዚአብሔር እረሲ መድኃኒተ ወእገሐድ ቦቱ ፤ ስለ ድሆች መከራ ስለ ችግረኞችም ጩኸት እግዚአብሔር አሁን እነሣለሁ ይላል" ሲል ክርስቶስ ስለሰዎች ድህነት መከራን ተቀብሎ ከሞተ በኋላ ከሞት እንደሚነሣ በትንቢቱ አረጋግጦ ነበር ።

ክርስቶስ ራሱ ከቅድስት ድንግል ተወልዶ በዚህ ዓለም በሚመላለስበት ዘመን እንደሚሞትና እንደሚነሣ ለደቀ መዛሙርቱ ሲነግራቸው እንደነበር በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 16፡21 ላይ ከዚያን ቀን ጀምሮ ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም ይሄድ ዘንድ ከሽማግሌዎችና ከካሕናት አለቆች ከጸፎችም ብዙ መከራ ይቀበልና ይገደል ዘንድ በሶስተኛውም ቀን ይነሣ ዘንድ እንዲገባው ለደቀ መዛሙርት ይገልጥላቸው ጀምር" የሚል ቃል ተጽፏል እንዲያውም ይህ ሁኔታ ደቀ መዛሙርቱን አሳዝኗቸው "ይህ አይሁንብህ ይህ ከቶ አይድረስብህ" ብሎ ቅዱስ ጴጥሮስ በመናገሩና ሐሳቡን በመቃወሙ "አንተ ሰይጣን የሰውን እንጂ የእግዚአብሔርን አታስብምና እንቅፋት ሆነህብኛል" ሲል ክርስቶስ እንደገሰፀው ቃሉ ያስረዳል በሌላ በኩል ደግሞ ዮናስ በአሣ አንበሪ ሆድ ሦስት መዓልት ሦስት ሌሊት እንደ አደረ ክርስቶስም በከርሠ መቃብር ሦስት መዓልትና ሌሊት አድሮ ይነሣል። ሲል ጊዜውንና ሰዓቱንም ጭምር ወስና እንደተናገረ በዚሁ በማቴዎስ ወንጌል እናነባለን፡ እንግዲህ ይህ ሁሉ የሚያስረዳው ሁሉ በሥልጣኑ ሥር ሁሉም በፈቃዱ ክልል ውስጥ ሆኖ የሚገዛለት ኃያል አምላክ እንደመሆኑ መጠን በራሱ ፈቃድ ሞቶ በራሱ ፈቃድና ሥልጣን እንደሚነሣ አስቀድሞ የሚያስገነዝብ ቃል ነበር ።

ትንቢቱ አልቀረም ጊዜው ሲደርስ ክርስቶስ ምንም ዓመፅ ሳይኖርበትና ምንም ዓይነት ወንጀል ሣይሠራ በአይሁድ አለቆችና ጭፍሮች ተይዞ በሽፍቶች መካከል ተሰቅሎ እንዲሞት ተደረገ ከብዙም መከራ በኋላ "ተፈጸመ" በሚል የመጨረሻ ቃል ቅድስት ነፍሱን ከቅዱስ ሥጋው በገዛ ፈቃዱ ለይቶ ራሱን ለሞት ሰጠ ነገር ግን ምንም እንኳን ስለኛ ኃጢአት ቢሣ ሊሆንን የኛን ደካማ ሥጋ ቢዋሐድም የኃያላን ኃያል የሆነ ፍጹም አምላክ ነውና አስቀድሞ የተነገረው ትንቢትና እሱም በሕይወተ ሥጋ በነበረበት ወቅት ለደቀ መዛሙርት የተናገረው ቃል ይፈጸም ዘንድ ልክ በሦስተኛው ቀን በመንፈቀ ሌሊት ሞትን ድል አድርጎ በራሱ ሥልጣን ተነሣ ወደፊት በመጨረሻው ዘመን በክብር እንነሣለን ብለን ተስፋ ለምናደርግለትም ተስፋ ትንሣኤ በኩር ሆነ ስለዚህ ነው "ትንሣኤው ትንሣኤያችን ነው" ብለን በፍጹም ተስፋ የምናመሰግነው ።

የክርስቶስ መነሣት በትንቢት መነገሩ ብቻ ሳይሆን በብዙ ሁኔታዎች ተረጋግጦ ትክክለኛ ምስክርነትን አግኝቷል፡

1ኛ. ማርያም መግደላዊት ድንጋዩ ከመቃብሩ ተፈንቅሎ በማየቷ "ጌታን ከመቃብር ወስደውታል ወዴትም እንዳኖሩት አናውቅም" ብላ ለቅዱስ ጴጥሮስና ለዮሐንስ ወልደ ነጐድጓድ በነገረቻቸው ጊዜ ወደ መቃብሩ ገብተው ማንኛውንም ሁኔታ ከተመለከቱ በኋላ አስቀድሞ ከሙታን ይነሣ ዘንድ በመጽሐፍ የተነገረው እውነት እንደሆነ አምነዋል ።

2ኛ. ይቺው መግደላዊት ማርያም ተስፋ ሳትቆርጥ በመቃብሩ አጠገብ ቆማ ስታለቅስ የኢየሱስ ሥጋ አርፎበት በነበረው በመቃብሩ አንዱ በራስጌ ሌላው በግርጌ ሆነው ተቀምጠው የነበሩ መላእክት ነጫጭ ልብስ የለበሱ መሰለው አንቺ ሴት ለምን ታለቅሻለሽ ባሏት ጊዜ "ጌታን ወስደውታል ወዴትም እንዳኖሩት አላውቅም ስትላቸው ወዲያውኑ ኢየሱስ ተገልጦ « ማርያም» ብሎ ጠርቶ በግልጥ እንዳነጋገራት ተጽፏል አስቀድሞም መላእክቱ "ሕያውን ከሙታን መካከል ስለምን ትፈልጋላችሁ እነሆ እሱ ተነሥቷል እንጂ በዚህ የለም ። የሰው ልጅ እንደሚሞትና በ3ኛውም ቀን እንደሚነሣ አስቀድሞ ለናንተ እንደተናገረ አስቡ" ብለው እንደነገሯቸው ቅዱስ ሉቃስ በ24ኛው ምዕራፍ ላይ ጠቅሶታል ።

3ኛ. ከትንሣኤው በኋላ ደቀ መዛሙርቱ በዝግ ቤት ሣሉ በተከታታይ ሁለት ጊዜ እንደገናም በጥብርያዶስ ባሕር አጠገብ በግልጥ ታይቶ በቃሉ አነጋግሮ በግልጥ መታየቱ መነሣቱን በፍጹም እንዲያምኑ አድርጓቸዋል ። ዮሐ. 20፡21 ።

4ኛ. ክርስቶስ በተነሣ ጊዜ ታላቅ የምድር መነዋወጥ ሆኗል መቃብሩን የሚጠብቁትም ጭፍሮች ደንግጠው እንደሙትም ከመሆናቸውም በላይ በኋላ ወደ ከተማ ወጥተው የሆነውን መስክረዋል ማቴ. 28፡1- 15።

ታዲያ ይህ ሁሉ ስለሰው ልጆች ደህንነት ሲል በራሱ ሥልጣን በአይሁድ እጅ ተሰጥቶ እስከሞት ድረስ የወደደን ክርስቶስ በመጨረሻው ጊዜ ሞትን ድል አድርጎ በራሱ ሥልጣን መነሣቱን የሚያስገነዝብ ነው ስለዚህም "ትንሣኤክ ለእለ አመነ ብርሃነክ ፈኑ ዲቤነ" ብሎ ቅዱስ ያሬድ እንዳመሰገነው እኛም ትንሣኤህን ለምናምን ሁሉ ብርሃንህን ላክልን እያልን በራሱ ሥልጣን የተነሣውን ክርስቶስን ዘወትር ልናመሰግነው ይገባል ።

ኢሳይያስ ወንድማገኘሁ

---

## ሳይንስ የከፈኑን .......

ከገጽ ፲፫ የዞረ

ያዙ ፡ የታጠፈውን ጨርቅ በማላላት (በሴት መነኮሳት በ16ኛው ክፍለ ዘመን የተጣፈውን ጨርቅ በማላላት ከከፈኑ በስተጀርባ ምን እንዳለ አዩ ። የቱሪን ባዮሎጂስት ጆቫኒሪጉ በፊበር ኦፕቲክስ ( Fiber Optics ) በተባለ መሣሪያ በመጠቀም የጨርቁን ኋላ ገጽ ፎቶ አነሣ ጥቃቅን ነገሮችንም ሰበሰበ ። በተጨማሪም ክሮች ተወስደዋል ።

### መርማሪዎች መረጃውን መተንተን ጀመሩ

አስደሳች ፡ ነገር ግን በጣም አድካሚ ቡድኑ ሥራውን የጨረሰው ዓርብ ማታ ነው ከፈኑ በቀይ ሐር ተጠቅልሎ በብር በተለበጠ ሣጥን ለመቶ ዓመታት ያህል ተቀምጦበት ወደነበረው ያጌጠ ካቴድራል ተመለሰ በዕብነበረድ በተሠራው መሠዊያ ከፍ ብሎ ከመስታዋት በተሠራው መስኮትና ከማገጃው ብረት በስተኋላ ቀረ ።

ወደ አገራቸው እንደ ተመለሱ በቤተ ሙከራዎቻቸው (ላቦራቶሪ) ከስድስት ቶን መሣሪያዎች ጋር አባሎቹ አድካሚ የሆነውን ተግባራቸውን በማከናወንና መረጃውን ፤ ፎቶግራፎችንና ለአይነት የተወሰዱትን ነገሮች በመተንተን ማጥናት ጀመሩ ሥራው ረጋ ያለ በትርፍ ጊዜም ላይ የተመረኰዘ ነው ። ዛሬ አንድ ዓመት ተኩል አልፎታል አብዛኛው ሥራ በመካከል ተስፋ የሚያስቆርጡና የሚቃረኑ መረጃዎች አሉበት ነገር ግን ለእንቆቅልሹ መፍቻ ሊቀርቡ የሚችሉ ብዛት ያላቸው አዳዲስ መረጃዎች እየመጡ ናቸው ።

የምስሉ ሁኔታ ምንድን ነው ? አጉልቶ በሚያሳይ መነጽር ምስሉ ባለበት አካባቢ የክሩ የላይኛው ክፍል ብሩህ የሆነ ብጫ ቀለም እንደሚያሳይ ሳይንቲስቶች ሪፖርት አቅርበዋል ። ቅቡ፤ሥዕሉ ወደ ሌለበት አቅጣጫ አልተሠራጨም ። ወይም ክሩን በሙሉ አላራሰውም ምንም የተወው ክምችት በክሩመሀከል የለም ። አንድ ሰው እንደሚገምተው ቀለም ከማንኛውም አይነት ነገር ላይ ቢቀባም የሚያሳየውን አይነት ጠባይ አላሳየም ።

እዚህ ላይ በ1532 ዓ.ም. በከፈኑ ላይ ደርሶ የነበረው የእሳት ቃጠሎ ለጥናቱ ፍንጭ ሰጥቷል አንዳንድ ሳይንቲስቶች ክሩን ለማቃጠል (ለማጥቆር) በቂ የሆነ ሙቀት ቀለሙን መለወጥ እንደነበረበትና የቀለሙም ለውጥ በተቃጠለው አካባቢ ከፍተኛ መሆን እንደነበረበት ይናገራሉ ብጫው ቀለም በሚያስገርም ሁኔታ እስከ ተቃጠለው ጠርዝ ድረስ አቅልሞታል ። እስከ አሁን ድረስ አልተለወጠም ። በተጨማሪም በከፈኑ ላይ እሳቱን ለማጥፋት የፈሰሰው ውሃ ቀለሙን ሊለውጠው (ሊያደበዝዘው) ይችል ነበር ። ይህ ሁኔታ በትክክል ሊሆን አልቻለም ።

በእነዚህ ዕውነታዎች ሳይንቲስቶች ከአንድ ጠለቅ ካለ መደምደሚያ ላይ ደርሰዋል ።

ኬምስትሬይ ሮጀርስ የሎስ አለምስ ብሔራዊ ሳይንሳዊ ቤተ ሙከራ ባልደረባ የሆነውሲያጠቃልል እንዲህ ብሏል ፡ "ከፈኑ ሥዕል እንዳልሆነ አብዛኞቻችን አምነናል ። በ1532 ዓ.ም. በደረሰው የእሳት ቃጠሎ ከፈኑ የነበረበት የብር ሳጥን ሲቃጠል ከተንጠባጠበበት ዝገት መሰል ነገር በስተቀር ምንም የቀለም አይነት አላገኘንም የምናየው ምስል በፈሳሽ ነገር ወይም በማንኛውም አይነት የሥዕል መሣሪያ ተሠራ ብለን አናስብም ።

የአንድ ቡድን አባል የቺካጎው ማይክሮስኮፒስት ( Microscopist ) ሲማክሮን አጉልቶ በሚያሳይ መነጽር ረዳትነት ሊታዩ የሚችሉ የብረት ውጉድ ከብጫው ክር ጋር ብዙዎቹ ተጣብቀዋል በዚህ ላይ በመመርኰዝ አንድን መላምት አቅርቦ ሲገልጽም በመጨረሻ የተከፋፈሉት ነገሮች በብዛት ብረት ያለው ከአርቲስቶች የጭቃ ቀለም ጋር ተመሳሳይ ነው ። እንደ ቀይ (አፈርማ ቀለም) ይህ ነገር አንድ ጊዜ ምስሉን ለማድመቂያ ተጠቅመውበታል ብሎ






www.ethiopianorthodox.org

ሐሳብ አቀረበ ። በብዙ ሳይንቲሳቶች ዘንድ ይህ መላምት ተቀባይነትን አላገኘም ።

አንድ የሌላ ቡድን አባል የሆነ የብርሃንን ጨረር የሚመረምር ሊቅ (ስፔክትሮስት) ( Spectroscopist ) የሳንታባርባራ የጥናት ማዕከል አባል የሆነው ሳሙኤል ፒሊኮሪ ሌላ አንድ መላ ምት አቅርቧል ፣ እርሱ እንዳለው ከሆነ ምስሉ የተሠራው ለረጅም ጊዜ በሰውነት ዘይት፡ ላብ ወይም ቅመማቅመም እንደ ጥሩ ሽታ በማጥቆር ነው ። ይህ እንግዲህ ምስሉ በእሳት ወላፈን መገረፉን ነው ። በእርግጥ ምስሉ በሙከራዎቹ የሚያመለክተው ላይላዩን በእሳት የተቃጠለው ቦታ የተጎዳው በ16ኛው ክፍለ ዘመን ቃጠሎ ነው ።

የእሳቱ ወላፈን ቢገርፈውም በቃጠሎው ምክንያት ቀለሙ አልተለወጠም ደግሞም የእሳቱ ወላፈን በገረፈው ላይ ውሃ ቢፈስበት ቀለሙ ሊደበዝዝ ወይም ሊለቅ አልቻለም ። የልብ ለባው ክዋኔ ምንም ነገር ቢያመጣም ከከፈኑ ላይ የምናየውን አስደሳች ምስል እስከ ታል ዳያን ሶረን ከተልባ እግር የተሠራ ጨርቅ ለዓይነት ከከፈኑ መሥሪያዎች ጋር የተመሳሰለ አግኝቶ ግማሹን በሳፖናርያ በከፈኑ ላይ የሚታዩትን አንዳንድ ነጠብጣብ በሚያስለቅቅ ንጥረ ነገር አጠበው ግማሹንም እንደዚሁ ተወው ከዚያ በኋላ በጥቂቱ እሳት አስነካው ስለዚህ ከፈኑ በሳፖናርያ ታጥቦ ቢሆን ኖሮ ልብለባው በቀላሉ ያጠቃው ነበር።

በሌላ መንገድ ሳፖናርያ አስፈላጊ እንደሆነ አረጋግጦአል ለአነስተኛ ሕይወት መርዛም ነው ፀረ እንጉዳይም ነው ። ምንም እንኳ ከፈኑ ለረጅም ጊዜ ተቀምጦ የነበረው በሻገተና ርጥበት ባለው ቤተ ክርስቲያን ቢሆንም ምንአልባት ከዚህ የተነሣ ይሆናል ብል ሳይበላውና ጉዳት ሳያገኘው ሊኖር የቻለው ።



ከፈኑ የጌታን ምስል እንዴት ሊያስቀር እንደቻለ ለመረዳት ተመሳሳይ መጠን ባለው ሰው እየለኩ ሲመራመሩ

ሊሆን የሚችለው ምስሉ በንክኮሽ የተሠራ እንደሆነ ነው ። የብርሃናዊው ጨረር መረጃ የእርሱን ሀሳብ የሚደግፍ ይመስላል ። ነገር ግን እንደ ሌሎች የቡድን አባሎች አመለካከት "እንዲህ አይነት ምስል ሦስት አቅጣጫ ያለው አይነት ሊሆን አይችልም" ብለዋል ። በተጨማሪም የምስሉ ገጽታ በዝርዝር የሚያመለክተው ሳይንቲስቱ እንደአለው ሳይሆን በፊት ለፊቱ ጨርቁ እንዳልተነካካ ነው ።

## የእንቆቅልሹ መፍቻ ይሆናል የተባለው መግለጫ

ከዚህ በኋላ ምስሉን ለመግለጽ ምን ቀረ ? በዚህ ነጥብ ላይ ከተለያዩ መሣሪያዎች የተገኘ ፍልጋ እንደ አመለከተው አሁን ድረስ መግለጽ አልተቻለም ። ከአንድ በኩል ገጽታ ብርሃን የልብለባ መላ ምት ከሬይ ሮጀርስና ከረዳቱ ዳያን ሶረን ወጣ እነርሱም ለምርምር ከሰበሰቡአቸው መጻሕፍት መካከል ከጥንታዊው የሮማ ታሪክ ጸሐፊ ስፒሊኒ መጽሐፍ ክሮችን ለማጠብና ለማለስለስ የሚያገለግለው ስትሪዩን ( Struthion በመባል የሚጠራው ነገር አጠቃቀም እንዴት እንደሆነ የሚገልጽ መረጃ አገኙ አንዳንድ ምንጮች እንደሚያመለክቱት ሸማኔዎች የላላውን ክር ለማጠንከር በባዚቃ ወይም በሙቃ ሙቅ ይነክሩታል ከዚያ በኋላ ጨርቁን በሳፖናርያ ( Saponaria ) እስኪለቅ ያጥቡ

## ጥያቄዎቹ ብዙ መልሶቹ ጥቂት

"ደሙ በውነት እውነተኛ ደም ነው? በደሙ የተበከለውና ምስሉ የተለያዩ መሆናቸው ግልጽ ሆኖ ቆይቶአል ። ይህንን እውነት ( Negative Plates ) (ከነጌቲቩ ፕሌት) ከፊልም ሲመለከት ያገኘው ሰኮንዶ ፒያ ነው ። (ከነጌቲቩ ከፊልሙ ላይ የደሙ አካባቢ ቦታ የሚያሳየው ነጭ ከከፈኑ ላይ በደም የተበከለው አካባቢ ትክክለኛ መልክ እንደሆነ ሲያረጋግጡ የአካሉ ምስል ግን እንዳየነው ከሆነ ፊልም ከመታጠቡ በፊት የሚያሳየውን ቅርጽ እንደያዘ ነው ።

የሳይንሳዊው ቡድን በቁሪን ሌላ ዓቢይ የሆነ ልዩነት በደሙና በምስሉ መካከል አገኘ የተጣፈውን ጨርቅ በሚያላቅቁበት ጊዜ የማጣበቅ ጠባይ ያለው ፈሳሽ ደሙ በፈሰሰበት ቦታ ጠቅላላ የተልባ እግሩን ጨርቅ ሠርፆ ገብቷል እስከአሁን በስተጀርባ በኩል የአካሉ መልክ አይታይም ። ሁለቱቦታዎች ማለት በደም የተበከለውና የአካሉ ቅርጽ ያረፉት በጠቅላላው በአንዳንድ የተለያየ መንገድ መገኘታቸው ግልጽ ነው ።

ደሙ ደም እንዳይደለ ያስተባበለ አንድም ሙከራ የለም ። በሌላ መንገድ በብዙ ሙከራዎች ሊሆን እንደሚችል ሀሳብ ቀርቦአል ። በኤክስሬይና በአልትራቫዮሌት ጨረር ስርጭት ረዳትነት የተበከለው ክፍል ደም መሆኑን ያመለክታል በተጨማሪም የኤክስሬዩ ውጤት ሙሉ በሙሉ በሰው ደም ውስጥ ሊኖር የሚገባው የብረት ማዕድን እንዳለበት በትክክል ያመለክታል ።

በመጨረሻም ዶክተር ዮሐንስ ሄለር የኒው ኢንግላንድ ኢንስቲትዩት ባልደረባ ከቀጭን ረጅም ጨርቅ ላይ የምታብለጨልጭ ነገር በጊዜ ብዛት የተለወጠች ሄሞግሎቢን ነው ብሎ የተቀበለውን ከቀጭን ረጅም ጨርቅ ላይ ፍርስራሽ አገኘ ። ያ የሚያብለጨልጨው ነገር ደም ነው ብሎ አምኖበታል ። ሌሎች የቡድን አባሎች በጥያቄው ላይ ተከፋፍለው የሌላ ሙከራ ውጤት እየተጠባበቁ ነው ።

የከፈኑ ዕድሜ ምን ያህል ይሆናል ? ከሁሉም ግልጽ የሆነው ጥያቄና እስከ አሁንም ያልተነካ ነው ፤ ( Radio-Carbon-dating ) . . . . . . . . . .

የራድዮ ካርቦን ዴቲንግ የጨርቁን ዕድሜ ይገልጥ ይሆናል ነገር ግን እስከዚህ አልተፈቀደም በራድዮ ካርቦን ሙከራ አንዳንድ ነገሮች ሊበላሹ ስለሚችሉና ባለሥልጣኖችም አብዛኛው የከፈኑ ክፍል ሊበላሽ ይችላል ብለው ስለፈሩ ነው ። ምንአልባት አሁን አንድ አዲስ ቴክኒክ ያንን ተቃውሞ ያገኘው ይሆናል ይህም በጣም ፈጣን በጣም ትክክለኛ መንገድ እንደማስ ስፔክትሮ ሜትር ( Mass Spectrometer ) የሚጠቁም አዙሪትም አለበት ።

ዶክተር ሐሪጐቭ የሮኬስተር ዩኒቨርሲቲ ባልደረባ እንዲህ አለ « በአንድ ስኴር ሳንቲ ሜትር (የትንሿን ጣት ሜፍ መጠን የምታህል) በመቶ ሃምሳ ዓመታት ውስጥ በማከታተል ትክክለኛ ዕድሜ ሊሰጥ ይችላል ። ነገሩን ካጣሩና ቆሻሻውን ካስወገዱ በኋላ እንኳ ቢሆን በቁ፡ ካርቦን ሙ ከራውን ብዙ ጊዜ ለመደጋገም ይቀር ይሆናል ።"

ምልክቶች ከቱሪን እንዳመለከቱት ከሆነ አሁን የቱሪን ሊቀ ጳጳስ በመጨረሻ ለካርቦን ዴቲንግ ፈቃድ ወደመስጠቱ አዘምብለዋል ።

ሁሉም ሙከራዎች ከፈኑ ጥንታዊ እንደሆነና በመጀመሪያው ዓ.ም. አካባቢ ነው ቢሉም እንኳ ገና ነገሩ ምሥጢር እንደሆነ ነው ። እንዴት ሦስት አቅጣጫ ያለው መግለጫ (ማስታወቂያ፣ በምስሉ ላይ ተቀዳ ምስሉ የተለበለበ ሲሆን እንዴት ሊወጣ ቻለ ? ሳይንቲስቶች አታላዮች ሊጠቀሙባቸው የሚችሉትን ቴክኒኮች ሁሉ ተመልክተዋቸዋቸዋልን? ከሁሉም በላይ ጥያቄው ይቀር ይሆናል ። ከፈኑ ክርስቶስ የተከፈነበት ነው ? ሁለቱም ማለት ሳይንቲስቶችና የነገረ መለኮት ሊቃውንት ይህብ ጥያቄ ዘለዓለም ከሰዎች ማረጋገጫ ውጭ ሁኖ ይቀራል ይላሉ ።

(ከናሽናል ጂዎግራፊ መጽሔት ቅጽ 157 ቁ. 6 ሰኔ 1980 በተማሪ ፈቃዱ ካሣ ተተረጐመ ።)

---

## ደብዳቤዎች .....

ከገጽ ፩ የዞረ

ም አንስቶ ወደላይ በተለያዩ መጠኖች ለማሸግ ከመርዳቱም በላይ ለማጓጓዝም ከሰው ኪስ አንስቶ እንዲሁ በተለያዩ መጠኖች ለማቅረብ ማስቻሉ ነው ። በተለይ ደግሞ በግለሰብም ሆነ በኅብረት ምእመናን እየገዙ ለቤተ ክርስቲያን ሊያበረክቱ የሚችሉ መሆኑን በመገመት ነው ። የመዋጮውን ገንዘብ ግን ከአዋጡት አድባራትና ከጠቅላይ ቤተ ክህነት የተመረጠ ኮሚቴ ተቋቋሞ የማስመጣቱና የማከፋፈሉ ተግባር በትክክል የሚካሄድ መሆኑንና የሒሳቡም አያያዝ ትክክል መሆኑን መቆጣጠር ያሻዋል ። ሌላው ሊታለፍ የማይገባው ነጥብ ደግሞ ሁሉም አብያተ ክርስቲያናት ከአዋጡት ጭምር እየከፈሉ መውሰድ ግዴታቸው ይሆናል ። የአዋጡትንም ገንዘብ እኒያ አድባራት ሊያገኙ የሚችሉት በእኔ ግምት ዘላቂው መፍትሔ ተግባራዊ ሁኖ አስተማማኝ ደረጃ ላይ ሲደርስና ፍሬ ሲሰጥ ብቻ መሆን ይገባዋል ። ለዚህም የአንድ ሰባት ዓመት ጊዜ መመደቡ ተገቢ ይመስለኛል ።

ዘላቂው መፍትሔ እንደሚከተለው ይሆናል ፤ በአደ አርቃይ ፣ በማኅበረ ሥላሴ በባሕር ዳር ፣ በጐንደር ፣ በዱከም ፤ በአሰቦት፣ ገዳምና በዝዋይ አካባቢ የወይን ተክል በመትከልና ማድረቂያውንም ማዘጋጀት ነው ። ቢሆንም ይህን ዕቅድ ተግባራዊ ለማድረግ አሁኑኑ አስቸኳይ ጥናት ማካሄድና ጥናቱም የወረቀት ብቻ ሳይሆን በሥራ ላይ እንዲውል ጠቅላይ ቤተ ክህነት ማትጋትና ኃላፊነቱንም መሸከም አለበት ።

ለዚህም የተቀደሰ ዓላማ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ተከታዮች በሙሉ የተሻለ ሐሳብ እንዲያቀርቡና የቤተ ክርስቲያናችንን ችግር እንዲያቃልሉ በእግዚአብሔር ስም ስጠይቅ ጠቅላይ ቤተ ክህነትም ይህን ችግር በመመልከት ጥሪውን እንዲያፋጥን አጥብቄ አሳስባለሁ ።

እንግዳ ወርቅ ጥሩነህ

አቶ እንግዳ ወርቅ ጥሩነህ ያቀረቡት አስተያየት ለቤተ ክርስቲያናችን እጅግ ጠቃሚ ስለሆነ የጠቅላይ ቤተ ክህነት ባለሥልጣኖች ተመልክተው እንዲያስቡበትና ምእመናንን እንዲያስተባብሩ አስተያየትዎን በሙሉ አውጥተነዋል ።





www.ethiopianorthodox.org

# የቤተሰብ ዓምድ

አዘጋጅ ንብረት አበበ

በዚህ የቤተሰብ ዓምድ በተሰኘው ዝግጅታችን ቤተሰብን የሚመለከቱና የቤተሰብን ሁኔታ የሚገልጹ ጽሑፎችን በማቅረብ አንዳንድ ቤተሰቦችን እናስተዋውቃችኋለን ።

በአሁኑ ዝግጅታችን የምናስተዋውቃችሁ አቶ ሣህሌ ገብሬንና ባለቤታቸው የሆኑትን ወ/ሮ አስፈች ኃይሌን እንዲሁም ልጆቻቸውን ነው ። አቶ ሣህሌ 53 ዓመት እድሜ ያላቸው ሲሆን ባለቤታቸው ደግሞ የ 45 ዓመት ወ ሮ ናቸው እኒሁ ሰዎች ኑሮን ከመመሥረታቸው በፊት የትውልድ ሀገራቸው 777 ኪ.ሜ. ያህል የሚራራቅ መሆኑን ሲገልጹ እንዴት ጋብቻቸውን ለመመሥረት እንደቻሉ እነሱንም ይገርማቸዋል ቢሆንም እግዚአብሔር ሁን ያለው ጊዜውን ጠብቆ ለመፈጸም የቦታ ወይም የዘመን እርቀት የማያውከው ስለሆነ በአንድነት ለመኖር እንደቻሉ ገልፀዋል።

አቶ ሣህሌ ይላሉ ለጥቂት ዓመታት ከቤተሰቦቼ ተለይቼ በሥራ ምክንያት ከቦታ ወደ ቦታ እየተዘዋወርኩ ሳገለግል እናቴ ከዚህ ዓለም በሞት ተለየች እኔም በዚህ ሥራዬ ላይ በብቸኝነት መኖሩ የማያዘልቀኝ መሆኑን በተረዳሁ ጊዜ አባቴን በኃዘኑና በቤተሰብ ረድኑት ላይ ዳረኝ ኳለኝ ብዬ ከማስቸገር ይልቅ ከምትመስለኝ ጋር ትዳር ይዤ መኖርን መረጥኩ አሁንም ባለቤቴ የሆነችዋ ወ/ሮ አስፈች ከላይ እንደተገለጸው የተወለድንበት ቦታ ይራራቅ እንጂ በዚያን ጊዜ ደግሞ በኑሮ ምክንያት እኔው በምኖርበት አካባቢ ትኖር ነበርበዚያን ጊዜም እርሷ ገና የ20 ዓመት ወጣት ነበረች ሰላምታ በመለዋወጥ ለጥቂት ዓመታት አሳልፈን ከዕለታት አንድ ቀን በሀሳቤ የተጠነሰሰውን የጋብቻ ጉዳይ አንስቼ አነጋገርኳት ለዘላቂ ዓላማ እንጂ በዕለታዊ ፍላጐት ተገፋፍቼ አለመሆኑንም ገለጽኩላት እሷም ልምከርበት በማለት ለጥቂት ጊዜያት ከቆየች በኋላ ቁርጥ ውሳኔ በማድረግ ፍቃድዋን ገለጸችልኝ በዚህ ጊዜም ወላ



አቶ ሣህሌ ገብሬና ቤተ ሰባቸው

ጆቿን ማስፈቀድ የሚያሻ መሆኑን ገለጽኩላት እሷም ወላጅ እናቷ እንደኔው እናት በሞት የተለዩ መሆናቸውን ገልጸ ምንም በብዙ ቤተ ዘመድ መካከል ብትኖርም ወሳኝ የሁለታችን ፈቃድ መሆኑን ገለጸችልኝ ። በዚህም መሠረት አማሩ ነገር ጨራሽ ፣ መልዕክተኛ ሌላውንም ሁሉ ሳንፈልግ ሁለታችን ለቁም ነገር ያሰብነው ጋብቻ ስለሆነ የእግዚአብሔር ቅዱስ ፈቃድ ይጨመርበት ብለን በሁለታችን ስምምነት ብቻ በ1943 ዓ. ም. የካቲት ወር ተጋብተን ትዳራችንን መሰረትን ። አሁን ትዳር ከያዝን 30 ዓመታችን ማለት ነው ታዲያ ከተጋባን በኋላ ለ5 ዓመታት ልጅ አልነበረንም እኛም ይህንን ነገር አላሰብንበትም ነበር ። የአክሱም ጽዮንን በዓል ለማክበር ሄደን ሳለ ሥርሐተ ሕዝብ ከሆነ በኋላ አንድ የዚያው አገር ኗሪ የሆኑ ወዳጃችን ለግብዣ ጠርተውን ሄደን ከምግብ በኋላ እዚያው ካሉት ሰዎች መካከል አንዱ ብድግ አለ እኛም ስለ ግብዣው ሊያመሰግን መስሎን በፀጥታ ስናዳምጥ ባለቤቴን እየጠቆመ ትወልዳለች ብለህ አታስብ እሷ እንደሆነች ደረቅ እንጨ

ወደ ገጽ ፳፪ ዞሯል




# ይህን ያውቁ ኖርዋል ?

እጅጉ ረታ

(ካለፈው የቀጠለ)

ከመጀመሪያው ጀምሮ እስከ መጨረሻ ድረስ ያለውንና የሚሆነውን የሚያውቅ ዘለዓለማዊ አምላክ በነቢያት አድሮ አስቀድሞ ባናገረው ትንቢት መሠረት ጢሮስ ልክ እንደ ትንቢቱ ቃል ተፈጽሞባት መጥፋቷን ፣ ከታሪክ ጋር በማገናዘብ በቁጥር 42 ትንሣኤ መጽሔት መገለጡ ይታወሳል ። በከፋቷ ፣ በበደሏ ምክንያት ትንቢት የተነገረባት ከተማ ይችው የጢሮስ ከተማ ብቻ አይደለችም ። ሌሎች አያሌ ከተሞችም አሉ ። ሁሉንም ከታሪክ ጋር እያገናዘቡ ማቅረብ ይቻል ነበር፡ ግን ጊዜም ቦታም ስለማይፈቅድ የጥቂቶችን ስም ብቻ በመጥቀስ እንደዚሁ አልፈዋለሁ። ‘‘ሲዶና’’ (ሕዝ. 28፥22-23) ‘‘መምፊስ’’ና ‘‘ቴቤስ’’ (ግብፅ) ሕዝ. 30፥13-16 ። ‘‘ቤቴል’’ ትን አሞጽ 3፥14-15



ከባቢሎን የከተማ ፍርስራሽ በከፊል

‘‘ባቢሎን’’ ወዘተ ---- እኒህና ሌሎችም ከተሞች በተሰጣቸው ማስጠንቀቂያ መሠረት ከበደላቸውና ፣ ከክፋታቸው ሳይመለሱ በመቅረታቸው ትንቢቱ እንደ ቃሉ በትክክል ተፈጽሞባቸዋል። ስለ ባቢሎን የተነገረው ትንቢት ግን ከሌሎቹ የተለየ ስለሆነ እንዲሁ ስሙን በመጥቀስ ብቻ መታለፍ ያለበት አይመስለኝም።ከሌሎቹየተለየ ያልኩበት፣ትንቢቱ በዘመነ ብሉይ የተነገረ የተፈጸመ ብቻ ሳይሆን ፣ በዘመነ ሐዲስም ተደግሞ የተነገረ ፣ የተፈጸመ ወይም ገና ወደፊት ይፈጸማል ተብሎ የሚጠበቅ ነውና ነው ።

ከክርስቶስ ልደት በፊት 750 ዓመት ገደማ ላይ የነበረው ፡ ከዐበይት ነቢያት አንዱ የሆነው ኢሳይያስ ፣ ስለ ባቢሎን ጥፋት እንዲህ ብሎ ትንቢት ተናግሮ ነበር « ...... ሰዶምና ገሞራን ባፈረሰ ጊዜ እንደ ነበረው ፣ የመንግሥታት ክብር የከላዳውያንም ትእቢት ጌጥ ባቢሎን እንዲሁ ትሆናለች።ለዘላለምየሚቀመጥባት አይገኝም ። ከትውልድ እስከ ትውልድ ድረስ ሰው አይኖርባትም ። በዚያ ድንኳን አይተክሉም ። እረኞችም መንጎቻቸውን በዚያ አያሳርፉም ። በዚያም የምድረ በዳ አራዊት ያርፋሉ ፡ ጉጉቶችም በቤቶቻቸው ይሞላሉ ። ሰጎኖችም በዚያ ይኖራሉ ኢሳ. 13 ቁ. 19-21’’ ሌላው ነቢይ ደግሞ በዚች የመከራ ድፍድፍ ተዘጋጅቶ በሚጠብቃት ከተማ ላይ የሚደርስባትን መከራ መንፈስ እግዚአብሔር በገለጠለት መሠረት እንደሚከተለው ተንብዮ ነበር ፣

‘‘....ከአንተም ለማዕዘን የሚሆን ድንጋይ አይወሰድም ፣ ለዘላለምም ባድማ ትሆናለህ ፣ ይላል እግዚአብሔር .51፥ 2 ዝቅ ይልናም « .....ከተሞችዋ ባድማና ደረቅ ምድር ፣ ምድረ በዳም ሰውም የማይቀመጥባት ፣ የሰውም ልጅ የማያልፍበት ምድር ሆኑ - .....’’ ቁጥር 43 ። ይላል ።

ከዚህ በላይ የተነገሩትን የትንቢት ቃላት በመልክ በመልኩ ስናስቀምጥ ባጭሩ እንደሚከተለው ይሆናል ።

ሀ ባቢሎን ወድማ እንደምትጠፋ ፡

ለ በምንም ዓይነት ዳግመኛ ተመልሳ ልትሠራና የሰው ዘር መኖርያ ለመሆን እንደማትችል ፣

ሐ እረኞች የበግ መንጎቻቸውን በዚያ እንደማያገደኙ ፣

መ ከተማይቱ የአራዊት መፈንጫ እንደምትሆን ፣

ሠ ከፍርስራሽ ላይ አንድ ፍሬ ድንጋይ ለሌላ ሕንፃ ሥራ ግልጋሎት እንደማይውል ፣

ረ እንዲህ ነበረች ብሎ ዘወር ብሎ ሊያያት የሚፈልግ ሰው እንደማይኖር ወዘተ.

ለመሆኑ ይህ ትንቢት የተነገረባት የባቢሎን ከተማ በዚያን ዘመን እንዴት ያለች ከተማ ነበረች ? ዛሬስ ምን ትመስላለች ? የባቢሎን ከተማ 2100 ዓመት ከልደት በፊት የባቢሎናውያን ( የሰናኦር ) መንግሥት መዲና ስትሆን ፡ ከነገሥታቱም አንዱ ሐሙራቢ ፣ እንደ አውሮፓ የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት አባባል አሞራፋኤል - ዘፍ 14፥1 የመጀመሪያውን የሕግ መጽሐፍ ያጻፈ መሆኑ በታሪክ ተመዝግቦለታል ይሁን እንጂ ነቢዩ ኢሳይያስ በሕይወት በነበረበት ዘመን 750 ዓመት ገደማ ከልደት በፊት ማለት ነው በዓለም ላይ ኃያሉ መንግሥት የአሶር መንግሥት ስለነበር የዚሁ መንግሥት ቅኝ ግዛት ነበረች ። ባቢሎን ታላቅና ገናና መንግሥት ሆና የተነሳችው 606 ዓመት ከልደት በፊት ሲሆን የወደቀችው 536 ዓመት ከልደት በፊት ላይ ነው።ስለዚህ ስለውድቀቷየተነገረውት



www.ethiopianorthodox.org

ንቢት በክብር፣በሥልጣን፣በኃይል ፣ በብልጽግና ከፍ ከፍ ከማለቷ ከመቶ ዓመት በፊት የተነገረ በመሆኑ ፣ ትንቢቱ በተነገረው መሠረት በትክክል ተፈጽሞ መገኘቱን ታሪክ አረጋግጧል።

606 ዓመት ከልደት በፊት ላይ የባቢሎን ከተማ እየሰፋች እየተዋበች ለመሄድ በቅታለች ። የቅጥሯ ዙሪያ ከብ 100 ኪሎ ሜትር ያህል ርዝመት ሲኖረው ፣ 90 ሜማ ውፍረት ፣ 300 ሜማ ቁመት እንደነበረው በጥንት የታሪክ ጸሐፊዎች ብርዕ ተወስቷል ። አቶ ከበደ ሚካኤልም በ1948 ዓ.ም. ባሳተሙት "የዓለም ታሪክ" በተሰኘው መጽሐፋቸው የዚያን ጊዜይቱ የባቢሎን ከተማ ከዛሬይቷ የፓሪስ ከተማ በስፋት ሰባት ጊዜ እንደምትበልጥ ጠቅሰውታል።መንገዶቿ ቀጥ ባሉ መስመሮች የተቀየሱ ሆነው ዳርዳራቸው በባለሶስትና አራት ፎቅ ቤቶች የተሠሩ ነበሩ ። ይልቁንም ከፍ ባሉ የፎቅ መደቦች ላይ አፈር ተደልድሎ የተሰሩት የአትክልት መናፈሻ ሥገነቶች (ዘሐንጊንግ ጋርደንስ) ከዓለም ሰባት ድንቅ ነገሮች እንደ አንድ ሆነው በመቆጠራቸው ስሟን በታሪክ ሲያስነሱት ይኖራሉ ። ይህች ከተማ 100 የሚሆኑ ጠንካራ ጠንካራ የነሐስ መዝጊያዎች የተገጠሙላትና ፣ በግንቡ አናት ላይ ሁለት መቶ አምሳ የዘብ ጥበቃ ማማዎች የተዘጋጁላት ስለነበረች በምንም ዓይነት ወራሪ ጠላት ይደፍራታል ተብሎ አይታሰብም ነበር ታላቁ የኤፍራጥስ ወንዝም ከተማይቱን መሐል ለመሐል ሰንጥቆ የሚያልፍባት በመሆኑ በውኃ በኩል ችግር አልነበረም ።ምድርዋ የሰጡትን ሁሉ የሚያበቅል ለም ስለነበረ ረሃብ ፣ ቸነፈር ያጠቃታል የማትባል ባሎር ቃል ሁሉ ተሟልቶ የተሰጣት ተድላ ደስታ ያለልክ የሚፈጸምባት ያስረሽ ምችው ከተማ ነበረች ታዲያ ችግር መከራ ያገኛታል ብሎ ያሰበ የጠረጠረ ማንም አልነበረም ። ትንቢቱ ግን ግድ መፈጸም ስለነበረበት 536 ዓመት ከልደተ ክርስቶስ በፊት የሜዶን ሠራዊት ዘምቶ አጥፍቷታል ። እዚህ ላይ እጅግ የሚያስደንቀው ከ214 ዓመት በፊት ፣ ኢሳይያስ በነበረበት ዘመን ገና ምኑንም ያልያዘችውና በመንግሥትነት ደረጃ ስሟ እስከዚህም ጐልቶ ያልታወቀ ሀገር ፣ ትንቢት ተነግሮላት ጊዜው ሲደርስ በድንገት ተነስታ በተነገረው ትንቢት መሠረት አንድም ቃል ሳይቀር በትክክል ተፈጽሞ ባቢሎንን ያህል የገናና መንግሥት ከተማ ለመጣል ሜዶን መብቃቷ ነው ። ኢሳ.13፣17-19። በኋላም ታላቁ እስክንድር የቀደሙ ክብሯን የቀደመ ገናናነትዋን ለመመለስ ቢጥርላትም ፣ ሊሳካላት አልቻለም ። ውድቀቷ እያቆለቆለ መጥቶ 100 ዓመት በዘመነ ሥጋዌ ለመጨረሻ ጊዜ ተንኮታኩታ ወድቃለች አሁን ያለችበት ሁናቴ ከእንግዲህ ወዲህ በምንም ዓይነት ተንሠራርታ ልትቋቋም ከማትችልበት ደረጃ ላይነው ።

እስከ ሰማይ ከፍ ከፍ ብላ የነበረችው ታላቋ ከተማ ፣ እነሆ ዛሬ ሰው የማይኖርባት ባድማና ደረቅ ምድረ በዳ ፣ የአራዊትም መፈንጫ ሆና ትገኛለች ። ያን ጊዜ የነበረውም የፍርስራሹ ድንጋይ እንዳለ በየቦታው ተከምሮ ይታያል ። መችም የጥንት ከተሞች ወይም ፍርስራሾቻቸው የሀገር ጐብኝ ዓይን ማራኪ መሆናቸው የታወቀ ነው ። የባቢሎን ከተማ የነበረችበትን ቦታ ግን ለማየት ዛሬ እግሩን ወደዚያ ለማንሳት የሚሻ አገር ጐብኝ እጅግ በጣም ጥቂት መሆኑ ይነገራል ።

እስካሁን ድረስ የተፈጸመባት ሁሉ ልክ በትንቢቱ እንደተነገረው ቃል በቃሉ ስለሆነ ለወደፊቱም ቢሆን ተመልሳ ተሠርታ የሰው ልጆች መኖሪያ ትሆናለች ተብሎ አይታሰብም ። የትንቢቱ ቃል ሊፈርስ አይችልምና ።

## ቤተ ሰብእ .....

ከገጽ ፰ የዞረ

ት ነች ደረቅ እንጨት ቅጠል እንደማያወጣ እንደማያብብ እና እንደማያፈራ ሁሉ እሷም አትወልድም ብሎ ዘላበደ እኛም በአነጋገሩ አዝነን በፈገግታና በዝምታ አልፍነው ይልቁንም ባለቤቴ በዚህ አነጋገር አዝናበት ኖሮ ወደ ማረፊያችን ከመሄዳችን በፊት ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄጄ ይህንን ሐዘኔን መግለጽ አለብኝ ስላለች አብረን ሄድን እንደደረሰችም "ያዘኑትን የምታጽናኚ የተበደሉትን የምትክሽ እመቤቴ ቅድስት ድንግል ማርያም ሆይ የአገልጋይሽን ልመና ሰምተሽ ልጅ እንደምትሰጪኝና ይህንን አውቃለሁ ብዬ ዘላባጅ እንደምታሳፍሪልኝ አምናለሁ" በማለት ብጽአት አድርጋ ወደ ማደሪያችን ተመለሰን ልክ በዓመቱም የምሥራች ወንድ ልጅ ወለደን እንደ ብጽአታችንም ክርስትናውን ለህዳር ጽዮን አክሱም ወስደን አስነሳን የልጃችንንም ስም የመጀመሪያውን ማለት ነው አምኃ ጽዮን አልነው እነሆም ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ስድስት ልጆች ወልደን "በሥጋ ወደሙ" ተወስነን እግዚአብሔር ለእያንዳንዳችን እስከሚሰጠን ዕድሜ ድረስ እንኖራለን ።

ከዚህ በፊትም በሰላም ፣ በፍቅርና በስምምነት ኖረናል ።

በነዚህ ዓመታት ውስጥ የባልና ሚስት አለመግባባት ውዝግብ ከቤታችን ገብቶ አያውቅም አንች ትብሽ አንተ ትብስ በመባባል እኔ ለሷ እሷም ለኔ በማሰብ እዚህ ደርሰናል ይልቁንም ባለቤቴ ለኔ የምታደርገውና በተግባርም የምታሳየው የማሰብና የመራራት ሁኔታ እናት ለልጅዋ ከምታደርገው ቢበልጥ እንጂ አያንስም ፍቅር የሞላበት ቤተሰብና ሰላም የሰፈነበት ትዳር ስለሰጠን ለእግዚአብሔር ምሥጋና እናቀርባለን ሲሉ አቶ ሣህሌ ላነጋገርናቸው መልስ ሰጥተውናል ።

አንባቢዎቻችን በአምዱ እናንተም ለመጠቀም ትችሉበት ዘንድ ለቤተሰብ ትምህርት ይሰጣል የሚል መልዕክት ካላችሁ በፖ.ሣ.ቁ. 3137 አ.አ. ብትልኩ ። በስልክ ቁ. 116616 ብተደውሉ መጥተን ለማነጋገር ዝግጅዎቹ ነን ።

## ሦስቱ መስቀሎች ....

ከገጽ ፲፭ የዞረ

ምሕረት ሲሰጠው «ዛሬውኑ አንተ ከኔ ጋራ በገነት ትኖራለህ » አለው ይህም አባባል በጎልጎታ የተላለፈ የመልእክቶች መልክት ተብሎ ሊጠራ ይገባል ። ይኸውም ወደ ገነት የሚወስደው መንገድ በኪሩቤልና በነበልባል ሰይፍ እየተጠበቀ ተዘግቶ ይኖር ነበር ኦሪት ዘፍጥረት ምዕ.3ቁ24 ስለዚህ በጎልጎታ በተተከለው መስቀል ላይ በፈሰሰው በክርስቶስ ደም የገነት በር ተከፈተ ክርስቶስ የጠፉትን ሊፈልግና ሊያድን በጎልጎታ ተሰቅሎአልና ሆኖም ወንበዴዎቹ የተሰቀሉባቸው ሁለቱ መስቀሎች ለቅጣትና ሌላውን ለማስፈራሪያ የቆሙ ሲሆኑ በመካከለኛው ተተክሎ የቆመው መስቀል ግን ለቅጣት ሳይሆን ስለ ዓለም ሕይወት መሆኑ በተግባር ተረጋገጠ ከኃጢአት ሁሉን ሊያድን የሚችለው በዚህ መስቀል የተሰቀለው ክርስቶስ ብቻ ነውና ።

ስለዚህም ኃጢአት ለብዙ ዘመን በሰማይና በምድር መሐከል ታላቅ የሞት ባሕር ፈጥሮ ይኖር ነበር በጎልጎታ ተተክሎ የቆመው መስቀል ግን የክርስቶስ መከራና ስቃይ ስለተፈጸመበትና በላዩም ላይ ክቡር ደሙ ስለፈሰሰበት ሰማውያንና ምድራውያንን አንድ አደረገ ሰዎችን ከእግዚአብሔር አስታረቀ ። ምንም እንኳን ጎልጎታ ለጊዜው የመከራና የኃዘን ቦታ ቢሆንም ለኃጢአተኞች መጠጊያ ከመሆኑም በላይ ወደ መንግሥተ ሰማያት መግቢያ በር ለማንም የተከፈተው በጎልጎታ በመሆኑ በመጨረሻ ለክርስቲያኖች ታላቅ ደስታ አስገኝቷል ለኃጢአት ፍጹም የሆነ መሥዋዕት የቀረበው ከኃጢአት የሚያነጻ ደሙም የፈሰሰው በጎልጎታ ነውና ።

በመጨረሻም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሆኖ «ሁሉ ተፈጸመ» አለ ። ይህንን ባለጊዜ የክርስቲያኖች መንፈሳዊ መብት ነፃነትና እኩልነት ፍጹም ሆነ ክርስቶስም በመስቀል ላይ ሆኖ የሰጠው የምህረት አዋጅና ያበሰረው መንፈሳዊ ነፃነት በቃል ሳይሆን በተግባር በመሆኑ ዘላለማዊ ደስታን ለአማኞች ይሰጣል ይህም የሥጋ ብቻ ሳይሆን የመንፈስም ነው ጊዜያዊ ሳይሆን ዘላለማዊ ነው ነፃነት ፣ መብት ፣ እኩልነት የሰው ማስተካከያ ሚዛኖች ሲሆኑ የተፈጸሙትም በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ደምና ሞት ነው ።

ስለዚህ ክርስቶስ ለኛ ነፃነትን ለመስጠት ራሱን ነፃነት እንደሌለው ሰው አደረገ ለኛም ሕይወት ለመስጠት ራሱን መሥዋዕት አደረገ።እኛም ባለ መብትና ባለ ስልጣን እንድንሆን ሲል እሱ ሥልጣንና መብት እንደሌለው ሆኖ በጲላጦስና በሄሮድስ ፊት ቆሞ ተወቀሰ ። ሁላችንም በሕይወት እንድኖርና ሕይወትም እንዲበዛልን ለኛ ሲል ሕይወቱን ሰጠ ስለዚህ ቬካናንድ የተባለው ሰው ሴቶች የገንዘብ አስተወጽኦ እያደረጉ ችግረኞችን እየረዱ ሕይወት ሲሰጡ አይቶ « የሀገሬ ሴቶች ሆይ መቶ ሕይወቶች ቢኖሩኝ በናንተ በኩል ያለብኝን የውለታ እዳ ለመክፈል ባልበቃኝም ነበር » ሲል ተናግሮአል እንዲያውም እኛም ብንሆን እያንዳንዳችን መቶ ሕይወቶች ቢኖሩን በክርስቶስ በኩል ያለብንን የውለታ እዳ ልንከፍል ባልቻልንም ነበር ።

ነገር ግን ክርስቶስ ከእኛ የሚፈልገው የሕይወት ለውጥ ሳይሆን ሞቱንና መከራውን እያሰብን ኃጢአታችንን ተሸክመን ወስደን ከመስቀሉ ስር እንድናስቀምጥነው « ሸክማችሁ የከበደ ወደኔ ኑ እኔም አሳርኳችኋለሁ » ብሎአልና ።

አለቃ ነቢየ ልዑል ዮሐንስ

# ወላዲተ አምላክ

ትንቢት አስነግሮ በመላእክት አብስሮ
ንጽሕናዋን ከመላእክት የእሷን አብልጦ
የሷን ሥጋ ለብሶ ፍጹም ሰው የሆነው
ከኃጢአት በቀር ጽድቅ የመሰረተው
በምድር ላይ እንደሰው የተመላለሰው
በገዛ ፈቃዱ ወደ ዓለም የመጣው ፤
ብዙ ተንገላቶ እንዲያ የተገረፈው
በመስቀል ላይ ሆኖ እጆቹን እግሮቹን የተቸነከረው
ጐኑን በጨካኞች በጦር የተወጋው
ውሀ ሲጠማው ሆምጣጤ የጠጣው
በደል ሳይኖርበት እኛን ለማዳን ነው ።
ከእግዝትነ ማርያም በለበሰው ሥጋ
ኃጢያታችንን ደምስሶ ሲያስገኝልን ዋጋ
ስለዚህ ሲምረን ይቅርም ሲለን
በመስቀል ላይ ሆኖ ተስፋ የሰጠን
ሌሎችም ቅዱሳት መጻሕፍት በሙሉ
ታላቁ መጽሐፍም የሚለውን አስተውሉ
እነሆ ልጅሽ እነኋት እናትህ(ዮሐ.19፣26
በማለት አደራ ለአንተ ያቀባበለህ
በክርስቲያንነትህ ክብር የተሰጠህ
በሥጋና በነፍስ ፣ ጸጋን ያጐናጸፈህ
በእመ አምላክ ነውና ሰው ሆይ ደስ ይበልህ
የእመብርሃንን እርዳታ ቃላትም አይገልጸው
እንደ ልጅዋ ሥራ እጹብ ድንቅ ብቻ ነው
መላእክት ይናገሩ ቅድስናዋን
ኪሩቤል ሱራፌል ንጽሕናዋን
ጻድቃን ሰማእታት ስለ ችሮታዋ
ያሬድና ኤፍሬም ስለ ምሥጋናዋ
ምእመናን ሌሎችም በሙሉ
ስለ እመብርሃን ይመስክራሉ
አሁንም በዚህ ዘመን እኛ በአለንበት
የሚድኑ ሰዎች በኪዳነ ምሕረት
ክርስቲያንም ሆነ ሌላም አማኝ ሁሉ
በእመ አምላክ እርዳታ ቶሎ ይድናሉ
የሚድኑት ድኅነት መች በሥጋ ብቻ
በነፍስም ጭምር ነው ምንም የለው አቻ
አባት ሆይ ማራቸው ይቅር በላቸው
የሚያደርጉትን የማያውቁ ደካሞች ናቸው
በማለት ይቅርታን እሱ የጠየቀው
ፍጹም ለበደሉት ላሰቃዩትም ነው
ስለዚህ ክርስቲያን የሆናችሁ ሁሉ
የበደላችሁን ይቅር እንድትሉ





www.ethiopianorthodox.org

እናንተ ይቅር በሉ ይቅር ትባላላችሁ
የሚለውን ትእዛዝ በተግባር ገልጸችሁ
ጠላቶቻችሁን ይቅር እያላችሁ
ለጸሎት ስትተጉ ቂም በቀል ትታችሁ
የፀሎታችሁ መልስ ወዲያውኑ ይመጣል
በመላእክትም ዘንድ ደስታ ይሆናል
ይህ የሕይወት መመሪያ ለእኛ ብርሃን ነው
ከጨለማ ለመውጣት ይቅርታን መውደድ ነው
ይቅርታን እንደሸማ የተጐናጸፋችሁ
በሥጋና በነፍስ ታላቅ ዋጋ አላችሁ
መላእክት ይደሰቱ በሰዎች ደህንነት
ጻድቃን ደናግል እንዲሁም ሰማእታት
ይቅርታ ሲደረግ ታላቅ ደስታቸው ነው
የድንግል ልመና የልጅዋ ፈቃድ
አንተን ያደርገሃል ምሕረት እንድትወድ
ነገር ግን ተፈጥሮ ጠላት ሲሆንብህ
አጅሬ ዲያብሎስ ከደት ሲፈጥርብህ
የተሰጠህ ተስፋ ከአንተ ይወሰዳል
ይልቁንስ በአምላክ ግመኑ ይበልጣል

በእመ አምላክ ፍጹም ረድኤት በእግዚአብሔር ፍጹም ቸርነት
ኢትዮጵያ ትቅደም

ከደብረ ገሊላ አማኑኤል እግዚአብሔር ምስሌነ ወጣቶች መንፈሳዊ ማህበር

ወጣት ሰሎሞን አጐናፍር

# የመጽሐፍ ቅዱስ ጥያቄዎች ውድድር መልስ

በቁጥር 42 በመጋቢት ወር 1973 ዓ.ም በዚህ መጽሔት ላወጣናቸው ጥያቄዎች ትክክለኛ መልሶቹን ለማወቅ ለምትሹ ቀጥሎ አቅርበንላችኋል

1.በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ 1189 ም ዕራፎች ይገኛሉ ።

2. በዘመነ ኦሪት እግዚአብሔር ለሰዎች ኃጢአት ማስተሰረያ የሰጠው መንገድ ፣ ሰዎች ለበደላቸው የበግ ወይም የፍየል መስዋዕት እንዲያቀርቡ ያዘዘው ነበር ። /ዘሌዋውያን 5፡6/

3.በዘፍጥረት መጽሐፍ.ም.24 የሚገኘው የአብርሃም ፣ የልጁ የይስሐቅ ፣የአብርሃም አገልጋይና የርብቃ ታሪክ ነው ታሪኩም የእግዚአብሔር አብ ፣ የእግዚአብሔር ወልድና የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ እንዲሁም የቤተ ክርስቲያን ነው ማለት ይቻላል ። /ዝርዝር ፍቺውን ለመስጠት ቦታ ያግዳል ።

4.በመገናኛው ድንኳን በርና በኋላም በቤተ መቅደሱ ውስጥ ቅድስቱን ከቅድስተ ቅዱሳን የሚለይ መጋረጃ ነበር።እርሱም በእግዚአብሔርና በሰው መካከል በኃጢአት ምክንያት የተፈጠረውን መለያየት የሚናገር ነበር ። በክርስቶስ ሞት መጋረጃው ስለተቀደደ ወደ አምላክ የሚወስደን መንገድ ተከፈተ ።

5. አይሁድ እንዲያከብሩዋቸው የታዘዙት ሰባት መንፈሳውያን በዓላት ነበሩ።

1. ሰንበት፡- እግዚአብሔር የፍጥረቱን ሥራ ፈጽሞ ያረፈበትና ሰዎችም እንዲያርፉበት ታዘዘ ።/ዘጸ. 20 ፡ 8-11/

2. ፋሲካ የቂጣ በዓል/ እስራኤል ከግብፅ ነፃ የወጡበት መታሰቢያ ዘጸ. 12 ፡ 1-20/

3. የመከር በዓል፡- የመከር አጨዳ መታሰቢያነት ያለው የምስጋና በዓል ዘጸ . 23፡ 16 ።

4ኛ የዳስ በዓል እህል ከተከማቸ በኋላ በዳስ የሚሰነብቱበት የምስጋና ሰሞን /ዘሌ. 23 ፡ 31 - 43/

5. የመለከት በዓል ፡- ለአዲስ ዓመት መባቻ መለከቶች የሚነፉበትና ያምልኮ ቀን ።

/ዘኁ. 29 ፡ 1-6/

6. የማስተሰረያ ቀን፡- ሰዎች ሁሉ ለበደላቸው ይቅርታ የሚለምኑበት ዕለት ።

/ዘሌ. 23 ፡ 26 - 32/

7. ፉሪም በመንግሥተ አስቴር አማካኝነት ከጠላቶቻቸው ወጥመድ የዳኑበት የደስታ በዓል ።

/አስ. 9 ፡ 16 - 28/

6. መላእክት ለሰው ልጆች ከሚያበረክቱአቸው አገልግሎቶች ፤

1. የእግዚአብሔርን ሰው በችግሩ ጊዜ ከጠላት ያወጣሉ ፡- ዘፍ. 19 ፡ 11፡ ዳን.3፡28

2. ከክፉ ይጠብቃሉ፡- መዝ. 91 ፡ 11

3. ሕፃናትን ይጠብቃሉ፡-ማቴ 18፡ 10

4. የተቸገሩትን ይመራሉ፡- ሉቃ. 24 ፡ 4

5. የእግዚአብሔርን መልእክት ለሰው ያስተላልፋሉ፡- የሐሥ. 27 23

7.ጥቅሶቹ የሚገኙበት መጽሐፍ

1. "አፍህን ስለዲዳው ክፈት" ምሳ 31 ፡ 8

2. "ተስፋ የሌለው ሰው ንግግር እንደነፋስ ነው ። " ኢዮ. 6 ፡ 36

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር

ናይ መ. ሣ. ቁ. 1252
ስልክ 158233
አዲስ አበባ

ናይ መ. ሣ. ቁ. 700
ስልክ 113455
አሥመራ



# ኢ.ኦ.ተ.ሐ.ድ

ማሳሰቢያ ለምእመናን በሙሉ

የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፣ ጸዋትወ ዜማዎችንና ቅዳሴዎችን ፡ መንፈሳዊ ዘመናዊ መዝሙሮችን ፣ ትምህርቶችንና የልማት እንቅስቃሴዎችን ሁሉ እየተከታተለ በቴፕ እየቀረጸ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ቋሚ ቅርስ ያስቀምጣል ። ይህንኑ ለሚፈልጉ ግለ ሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች የካሴት ክር ላቀረቡ ያገልግሎት ሁለት ብር ብቻ በማስከፈል ይሰጣል ።

ለዚሁ ጥያቄ ቢኖርዎ ከድርጅቱ በመምጣት ወይም ስልክ በመደወል ለመረዳት ይቻላል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሐዋርያዊ ድርጅት
የካሴት ሐዋርያ አገልግሎት

ስልክ ቍ. 116616
የመል. ሣ. ቍ. 3137
አዲስ አበባ

www.ethiopianorthodox.org